https://chilot.me

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፬
አዲስ አበባ ጥር ፲፯ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

28th Year No.4
ADDIS ABABA 25th January, 2022

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፷፫/፪ሺ፲፬

የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ……………………………………..ገጽ ፲፫ሺ፯፻፶፩

**Content**

Proclamation No. 1263/2021

Definition of Powers and Duties of the Executive Organs Proclamation ……...................................................Page 13751

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፷፫/፪ሺ፲፬

## <u>በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል መንግሥት አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ</u>

ተቋማት ሲደራጁ የተሰጣቸውን ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት በሚያስችል መልኩ ግልጽ ዓላማ ያላቸው፣ ከሌሎች ተቋማት ሥልጣንና ተግባር ጋር የማይጋጭና ተናባቢ የሆነ ተግባርና ኃላፊነት እንዲኖራቸው በማድረግ፣ በቅንጅት የሚሰሩ፣ ውጤታማና ወጪ ቆጣቢ የሆነ፣ ብክነትን የሚቀንስና ውጤታማነትን የሚያበረታታ፣ ኃላፊነቱን ሲያጓድል ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል የአስፈጻሚ አካላት አደረጃጀት መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የአስፈጻሚ አካላትን አደረጃጀት፣ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በየጊዜው የሚወጡ ሕጎች ወጥ የሆነ የተቋማት አደረጃጀትና ስያሜ ለመፍጠር ያልቻሉ በመሆኑ የተቋማት ቀጣይነትን ለማረጋገጥና የስያሜ ወጥነትን ለማስቀጠል ያልተቻለ በመሆኑ፣

## PROCLAMATION NO.1263/2021

## <u>A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE DEFINITION OF THE POWERS AND DUTIES OF THE EXECUTIVE ORGANS OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF EHTIOPIA</u>

**WHEREAS,** it has become necessary to establish an organizational structure that, allows coordinated work and, is efficient and cost effective, reduces resource wastages and ensure accountability by establishing government agencies with clear objectives that do not conflict with the powers and duties of other agencies and; which are cohesive in a manner that fulfills the duties and responsibilities entrusted to them;

**WHEREAS,** the laws that have been enacted to reorganize the organizational structure and define the powers and duties of the executive organ have not been able to establish sustainable reorganizational structures and designation of institutions and as a result it has become impossible to ensure the continuity of institutions and uniformity of designation;

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

https://chilot.me



በሥራ ላይ ያለውን የተቋማትን አደረጃጀትና ስያሜ ችግሮች በዝርዝር በጥናት በመለየት በየጊዜው የማይለዋወጥ፣ ዘላቂነት ያለው እንዲሁም ከማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ለውጥ ጋር አብረው እየተለወጡ የሚሄዱ የተቋማት አደረጃጀትና ስያሜን መፍጠር የሚያስችል ሥርዓት በሕግ መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፣

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል መንግሥት ሕገ-መንግሥታዊ ሥልጣንና ኃላፊነቱን በአግባቡ ለመወጣት የሚያስችለው አወቀቃቀር መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፷፫/ ፪ሺ፲፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪. ትርጓሜ**

በዚህ አዋጅ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፦

፩/ **"ሕገ-መንግሥት"** ማለት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት ነው፤

፪/ **"ክልል"** ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፵፯ የተካተተ ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደርን ይጨምራል፤

፫/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትም ፆታ ይጨምራል።

**WHEREAS,** it has become necessary to establish a system which enables to put in place a sustainability of organizational structure and designations that go with the evolving socio-economic changes by identifying the problems of the existing organizational structure through detail studies;

**WHEREAS,** it has become necessary to put in place an organizational structure that enables the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia to carry out its constitutional powers and duties;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

## PART ONE

## GENERAL PROVISIONS

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Definition of Powers and Duties of the Executive Organs Proclamation No. 1263/2021".

**2. Definition**

In this Proclamation, unless the context otherwise requires:

1/ **"Constitution"** means the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

2/ **"Region"** means any region referred to under Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes the Addis Ababa and Dire Dawa City Administrations;

3/ Any expression in the masculine gender includes the feminine.

https://chilot.me



## ክፍል ሁለት

## ስለጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ስለምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩና ስለሚኒስትሮች ምክር ቤት

### ፫. የጠቅላይ ሚኒስትሩ ሥልጣንና ተግባር

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር ሥልጣንና ተግባር በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ ፸፬ የተመለከተው ነው።

### ፬. የምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሥልጣንና ተግባር

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ሥልጣንና ተግባር በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ ፸፭ የተመለከተው ነው።

### ፭. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ ፸፯ የተመለከተው ነው።

### ፮. የሚኒስትሮች ምክር ቤት አባላት

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል:-

ሀ) ጠቅላይ ሚኒስትር፣

ለ) ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር፣

ሐ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፮ የተመለከቱትን ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች የሚመሩ ሚኒስትሮች፣ እና

መ) በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሰየሙ ሌሎች ባለስልጣናት።

## PART TWO

## THE PRIME MINISTER, THE DEPUTY PRIME MINISTER, AND THE COUNCIL OF MINISTERS

### 3. Powers and Duties of the Prime Minister

The powers and duties of the Prime Minister of the Federal Democratic Republic of Ethiopia are those defined under Article 74 of the Constitution.

### 4. Powers and Duties of the Deputy Prime Minister

The powers and duties of the Deputy Prime Minister of the Federal Democratic Republic of Ethiopia are those defined under Article 75 of the Constitution.

### 5. Powers and Duties of the Council of Ministers

The powers and duties of the Council of Ministers of the Federal Democratic Republic of Ethiopia are those defined under Article 77 of the Constitution.

### 6. Members of the Council of Ministers

1/ The Council of Ministers shall have the following members:

a) the Prime Minister;

b) the Deputy Prime Minister;

c) Ministers heading the Ministries specified under Article 16 of this Proclamation; and

d) Other Officials to be designated by the Prime Minister.

https://chilot.me



፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) ፊደል (ሐ) የተመለከተው ማንኛውም ሚኒስትር በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ ሊገኝ በማይችልበት ጊዜ የሚኒስቴሩ ሚኒስትር ዴኤታ በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ ይሳተፋል፤ ከአንድ በላይ ሚኒስትር ዴኤታዎች ካሉና ሚኒስትሩ በተለይ ካልወከለ በሹመት ቅድሚያ ያለው ሚኒስትር ዴኤታ በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ ይሳተፋል።

**፯. <u>የሚኒስትሮች ምክር ቤት የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት</u>**

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት፦

ሀ) ሥራውን በአግባቡ ለማካሄድ አስፈላጊው የውስጥ ደንብ ይኖረዋል፤

ለ) በውስጠ ደንቡ በሚወሰነው መሠረት መደበኛ እና አስቸኳይ ስብሰባዎችን ያካሂዳል፤

ሐ) ስብሰባ ላይ ከአባላቱ ከግማሽ በላይ ሲገኙ ምልዓተ-ጉባዔ ይሆናል፤

መ) የሚያስተላልፈው ውሳኔ በተባበረ ድምጽ ይሆናል፣ በተባበረ ድምጽ መወሰን ካልተቻለ በአብልጫ ድምጽ ይወሰናል፤ የተሰጠው ድምጽ እኩል ለእኩል የተከፈለ እንደሆነ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ያለበት ወገን ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።

፪/ ጠቅላይ ሚኒስትሩ፦

ሀ) የሚኒስትሮች ምክር ቤት አባላት አጀንዳ የማስያዝ መብታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ለምክር ቤቱ በአጀንዳ የሚቀርቡ ጉዳዮችን ይወስናል፤

ለ) የምክር ቤቱን ስብሰባ ይመራል፤

2/ Where any Minister of a Ministry referred to in Sub-Article (1) Paragraph (c) of this Article is not in position to attend the meeting of the Council, the Minister of State of the Ministry shall take part in the meeting of the Council. Where there are more than one ministers of state and no specific delegation has been given by the Minister, the Minister of State who is senior by appointment shall take part in the meeting of the Council.

**7. <u>Meeting Procedure of the Council of Ministers</u>**

1/ The Council of Ministers shall:

a) have its own internal rules of procedure for the proper conduct of its activities;

b) conduct ordinary and extraordinary meetings in accordance with its rules of procedure;

c) have a quorum where more than half of its members are present;

d) Pass decisions by consensus, or failing that, by majority vote; where the Council has given an equal number of votes for and against a decision, the Prime Minister shall have a casting vote.

2/ The Prime Minister shall:

a) determine, without prejudice to the rights of the members of the Council of Ministers, the agenda items to be tabled in the Council;

b) preside over the meetings of the Council;

https://chilot.me



ሐ) ለምክር ቤቱ በአጀንዳ የቀረበ ጉዳይ በሚመለከተው የምክር ቤቱ ኮሚቴ መታየት የሚያስፈልገው ሆኖ ካገኘው ስብሰባውን ለሌላ ጊዜ ያስተላልፋል፤

፫/ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በማይኖርበት ጊዜ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ የምክር ቤቱን ስብሰባ ይመራል።

**፰. <u>የሚኒስትሮች ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴዎች</u>**

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባሩን ለመወጣት ይረዳው ዘንድ የምክር ቤቱ አባላት የሚገኙባቸው ልዩ ልዩ ቋሚ ኮሚቴዎች ሊያቋቁም ይችላል፡፡

፪/ የቋሚ ኮሚቴዎች ሥልጣንና ተግባር በምክር ቤቱ የውስጥ ደንብ ይወሰናል።

## <u>ክፍል ሶስት</u>
## <u>የፌደራል አስፈጻሚ አካላት ስያሜ</u>

**፱. <u>ስለ ሚኒስቴር</u>**

አንድ ተቋም፡-

፩/ በዋናነት ሥራውን በሚያከናውንበት ዘርፍ እና በተያያዥ ጉዳዮች ላይ ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ እና ፕሮግራም የሚቀርጽ፤ ሲጸድቁም በበላይነት ተፈጻሚነታቸውን የሚመራና የሚያስተባብር፤

፪/ በሚሰማራበት ዘርፍ ሌላ ተቋም ስታንዳርድ በማውጣት ቁጥጥር የሚያደርግ፤ እንደአስፈላጊነቱ ፈቃድ የሚሰጥ፣ አቅም በመገንባት እንዲሁም በተጨባጭ ፕሮግራምን ወደ ፕሮጀክትነት በመቀየር የቀን ተቀን ሥራዎችን የሚያከናወን እና አገልግሎት የሚሰጥ፤

c) adjourn the meetings of the Council under circumstances where he finds it necessary to refer the matter included in the Council's agenda to the relevant Committee of the Council.

3/ In the absences of the Prime Minister, the Deputy Prime Minister shall preside over the meetings of the Council.

**8. <u>Standing Committees of the Council of Ministers</u>**

1/ The Council of Ministers may, with a view to discharging its powers and duties, establish various standing committees comprising of its members;

2/ The powers and duties of the Standing Committees shall be defined in the internal rules of the Council.

## <u>PART THREE</u>
## <u>NOMENCLATURE OF THE FEDERAL EXECUTIVE ORGANS</u>

**9. <u>Ministry</u>**

An institution that:

1/ Has the power to formulate mainly sectoral polices, strategies and programs and related matters and oversees and coordinate its implementation upon approval;

2/ Regulate sectoral activities by issuing standards; issuing license as may be appropriate, conduct day-to-day activities and provide service by building capacity as well as translating development programs into projects in a concrete manner;

https://chilot.me



፫/ ተጠሪ ለሆነለት ወይም እንደአስፈላጊነቱ ከሥራው ጋር ተያያዥነት ላለው ለሌላ የፌደራል ወይም የክልል ተቋም ከተሰጠው ሥልጣንና ተግባር በከፊል በውክልና የሚሰጥ፤

በሚኒስቴርነት ይሰየማል፡፡

## ፲. ስለ ኮሚሽን

አንድ ተቋም፡-

፩/ ለሚኒስቴር መስሪያ ቤት፣ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ወይም ለተወካዮች ምክር ቤት ተጠሪ የሚሆን፤

፪/ የተለያዩ መስሪያ ቤቶችን ሥራ የሚያቀናጅ፣ ፖሊሲን እና ስትራቴጂን የሚቀርጽና አፈጻጸሙን በበላይነት የሚያስተባብር እንዲሁም መስሪያ ቤቶችን የሚያስተባብር፤

፫/ እንደአግባቡ ዘላቂ ለሆነ ወይም በአንዳንድ ሁኔታ በጊዜያዊነት አንገብጋቢ ለሆኑ ጉዳዮች ሊቋቋም የሚችል፤

በኮሚሽንነት ይሰየማል፡፡

## ፲፩. ስለ ባለስልጣን

አንድ ተቋም፡-

፩/ የቁጥጥር፤ ደረጃ የማውጣትና በወጣው ደረጃ መሠረት መተግበሩን የሚያረጋግጥ፣

፪/ ለሚኒስቴር መስሪያ ቤት ተጠሪ የሚሆን ወይም ተጠሪ ከሆነለት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ሥራ ጋር የጥቅም ግጭት ይኖራል ተብሎ ሲገመት ለጠቅላይ ሚኒስቴር ወይም ለሌላ የመንግስት አካል ተጠሪ የሚሆን፤

፫/ በዋናነት በተሰጠው የዘርፍ ሥራ ስታንዳርዶችን የማውጣት፤ ስታንዳርዶችን መሠረት በማድረግ የቁጥጥር ሥራ የሚያከናውን፤ ወይም በሚመለከተው አካል የወጡ ስታንዳርዶችን የሚያስፈጽም፣

3/ delegate part of its powers and duties to the institution that is accountable to it or to other federal and regional institution related to its activities;

shall be designated as a Ministry.

## 10. Commission

A Commission that:

1/ Is accountable to a Ministry, the Prime Minister or the House of peoples' representatives;

2/ Coordinate the activities of different Executive Organ; formulate policies and strategies and oversees its implementation;

3/ Is established on a permanent basis or, under certain conditions, for urgent assignment on a temporary basis;

shall be designated as a Commission.

## 11. Authority

An institution that:

1/ Perform regulatory function; issue standards and ensure their compliance with same;

2/ Is accountable to a Ministry or, where there is a potential conflict with the activities of a institution to which it is accountable, to the Prime Minister other Government organ;

3/ Issue standards when required mainly in its sector and based on the standards perform regulatory functions; or implement standards issued by the concerned organ;

https://chilot.me



፬/ ፈቃድ የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ሲኖር ፈቃድ የመስጠት እና የመቆጣጠር ሥራን የሚያከናውን፤

በባለሥልጣንነት ይሰየማል፡፡

## ፲፪. አስተዳደር ወይም ልማት

አንድ ተቋም፡-

፩/ የልማት እና የመሠረተ ልማት ሥራዎችን እና አስተዳደርን በመደበኛነት የሚያከናውን እና በበላይነት የሚመራ፤

፪/ የመሠረተ ልማት ግንባታ፣ ጥገና፣ አገልግሎት አሰጣጥ እና አስተዳደር ለማከናወን ሌላ የመንግስት ልማት ድርጅትን ወይም የግል ድርጅትን በመጠቀም የተሰጠውን ኃላፊነት የሚወጣ፤

በአስተዳደርነት ወይም በልማትነት ይሰየማል፡፡

## ፲፫. አገልግሎት

አንድ ተቋም በዋናነት ለመንግስት አካላት አስፈላጊ የሆኑ አገልግሎቶችን በማዕከል ደረጃ ለመስጠት የሚቋቋም ወይም በዋናነት ለዜጎች አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም በአገልግሎትነት ይሰየማል፡፡

## ፲፬. ጽህፈት ቤት

አንድ ተቋም በዋናነት አንድን ልዩ ትኩረት የሚፈልግ ተግባር በልዩ ሁኔታ ተቋማዊ አደረጃጀት ይዞ የተለያዩ ተቋማትን ማስተባበር በሚያስፈልግት ወቅት በልዩ ሁኔታ ወጥነት ላለው ጊዜያዊ ወይም ቋሚ ዓላማ የሚቋቋም በጽህፈት ቤትነት ይሰየማል::

4/ Issue license for activity that required licensing and regulate the same;

shall be designated as an Authority.

## 12. Administration or Development

An institution that:

1/ Conduct on a regular basis mainly the development and Infrastructure development activities and oversee the same;

2/ Carry out its responsibilities by using the services of other public enterprises or private organizations for construction of infrastructure, maintenance of infrastructure, service delivery and management;

shall be established as an Administration or Development.

## 13. Service

An institution that is established mainly to provide centralized services necessary for Government organs or provide service mainly to citizens shall be designated as a Service.

## 14. Office

An institution that is established, for temporary or permanent purpose, under special circumstances to conduct mainly activities that require special attention and institutional arrangement by coordinating various institutions in a uniform manner shall be designated as an Office.

https://chilot.me


፲፭. **ኢንስቲትዩት**

አንድ ተቋም ተጠሪነቱ እንደተሰማራበት የሥራ ዘርፍ አግባብ ላለው ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ወይም ሌላ መስሪያ ቤት የሆነ በሥልጠና፣ በጥናትና ምርምር እና በማማከር አገልግሎት ላይ የሚያተኩር በተቋቋመበት ዘርፍ ልምድ እና ሙያዊ ብቃት ያለው አመራር ያለው በኢንስቲትዩትነት ይሰየማል፡፡

**ክፍል አራት**

**ስለሚኒስቴሮች መቋቋም፣ ሥልጣንና ተግባራትና የሚኒስትሮች ተጠሪነት**

**ንዑስ ክፍል አንድ**

**ስለሚኒስቴሮች መቋቋምና የሚኒስትሮች ተጠሪነት**

፲፮. **የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች መቋቋም**

የሚከተሉት ሚኒስቴሮች በዚህ አዋጅ ተቋቁመዋል፡-

፩/ የግብርና ሚኒስቴር፣
፪/ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣
፫/ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር፣
፬/ የማዕድን ሚኒስቴር፣
፭ የቱሪዝም ሚኒስቴር፣
፮/ የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር፣
፯/ የገንዘብ ሚኒስቴር፣
፰/ የገቢዎች ሚኒስቴር፣
፱/ የፕላንና ልማት ሚኒስቴር፣
፲/ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፣
፲፩/ የትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ሚኒስቴር፣
፲፪/ የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር፣
፲፫/ የውሃና ኤነርጂ ሚኒስቴር፣
፲፬/ የመስኖና ቆላማ አከባቢ ሚኒስቴር፣
፲፭/ የትምህርት ሚኒስቴር፣
፲፮/ የጤና ሚኒስቴር፣
፲፯/ የሴቶችና ማሕበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣

15. **Institute**

An institution that is accountable to the relevant Ministry or to other Government organ and that focuses on training, study and research and consulting services; and have experienced and professionally competent leadership in the sector shall be designated as an Institute.

**PART FOUR**

**ESTABLISHMENT OF MINISTRIES; POWERS AND DUTIES AND ACCOUNTABILITY**

**SUB SECTION ONE**

**ESTABLISHMENT OF MINISTRIES AND MINISTRIES ACCOUNTABILITY**

16. **Establishment of Ministries**

The following ministries are established by this Proclamation:-

1/ Ministry of Agriculture;
2/ Ministry of Industry;
3/ Ministry of Trade and Regional Integration;
4/ Ministry of Mines;
5/ Ministry of Tourism
6/ Ministry of Labor and Skill;
7/ Ministry of Finance;
8/ Ministry of Revenue;
9/ Ministry of Planning and Development;
10/ Ministry of Innovation and Technology;
11/ Ministry of Transport and Logistics;
12/ Ministry of Urban and Infrastructure;
13/ Ministry of Water and Energy;
14/ Ministry of Irrigation and Lowland;
15/ Ministry of Education;
16/ Ministry of Health;
17/ Ministry of Women and Social Affairs;

https://chilot.me



፲፰/ የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር፣

፲፱/ የመከላከያ ሚኒስቴር፣

፳/ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣

፳፩/ የፍትሕ ሚኒስቴር፣

፳፪/ የሰላም ሚኒስቴር፡፡

## ፲፯. የሚኒስትሮች ተጠሪነትና ኃላፊነት

እያንዳንዱ ሚኒስትር፡-

፩/ ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ይሆናል፤

፪/ የሚመራውን ሚኒስቴር ይወክላል፣ ሥልጣንና ተግባሩን ሥራ ላይ ያውላል፤

፫/ ለሚኒስቴሩ በተፈቀደው በጀትና የልማት ዕቅድና ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ መሆኑን ያረጋግጣል፤

፬/ በሚኒስቴሩ ውስጥ የአመራር አተገባበር ሥርዓት ተግባራዊ መደረጉን ያረጋግጣል።

## ፲፰. የሚኒስትር ዴኤታዎች ተጠሪነትና ኃላፊነት

፩/ የእያንዳንዱ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ተጠሪነቱ ለሚኒስትሩ ሆኖ የተመደበበትን ዘርፍ ተግባራት ያከናውናል፡፡

፪/ ሚኒስትሩ በማይኖርበት ጊዜ ሚኒስትር ዴኤታው ተክቶት ይሠራል፤ ከአንድ በላይ ሚኒስትር ዴኤታዎች ካሉና ሚኒስትሩ በተለይ ካልወከለ በሹመት ቅድሚያ ያለው ሚኒስትር ዴኤታ ተክቶት ይሠራል።

18/ Ministry of Culture and Sport;

19/ Ministry of Defense;

20/ Ministry of Foreign Affairs;

21/ Ministry of Justice;

22/ Ministry of Peace.

## 17. Accountability and Responsibility of Ministers

Each Minister shall:

1/ Be accountable to the Prime Minister and the Council of Ministers;

2/ Represent the Ministry, he runs and exercise its powers and duties;

3/ Ensure that payments are affected in accordance with the budget and work programs approved for the Ministry;

4/ Ensure the implementation of performance management system within the Ministry.

## 18. Accountability and Responsibility of State Ministers

1/ Each State Minister of a Ministry is accountable to the Minister and carry out the functions entrusted to the sector he is assigned to.

2/ In the absence of the Minister, the State Minister shall, act on his behalf; where there are more than one State Ministers and no specific delegation has been given by the Minister, the State Minister who is senior by appointment shall act on behalf of the Minster.

https://chilot.me


## ንዑስ ክፍል ሁለት

## የሚኒስቴሮች ሥልጣንና ተግባራት

### ፲፱. የሚኒስቴሮች የወል ሥልጣንና ተግባራት

እያንዳንዱ ሚኒስቴር በዚህ አዋጅና በሌላ ሕግ በተሰጠው ሥልጣንና ተግባር መስክ፡-

፩/ የጥናትና ምርምር ተግባራትን ያከናውናል፣ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያቀነባብራል፣ ያሰራጫል፤

፪/ በጥናት ላይ የተመሠረቱ ፖሊሲዎችን ያመነጫል፤

፫/ የፌደራል መንግሥት ሕጎችን ያመነጫል፣ ያስፈጽማል፤

፬/ በሕግ የተጣለበትን ተግባርና ኃላፊነቶች ለመወጣት የሚያስችለውን መመሪያ ያወጣል፤

፭/ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን በሥራ ላይ ለማዋል ከሌሎች ሚኒሰቴር መስሪያ ቤቶችና ተቋማት ጋር አስፈላጊውን ቅንጅት በመፍጠር ይሠራል፤

፮/ ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

፯/ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ያከናውናል፣ የለውጥና የመልካም አስተዳደር ሥራዎችን ይፈጽማል፣ ያስፈጽማል፣ ውጤታማነታቸውን ያረጋግጣል፤

፰/ ለክልሎች ወይም ለአካባቢዎች እንደአስፈላጊነቱ ድጋፍና ምክር ይሰጣል፤ ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ክልሎች ወይም አካባቢዎች ልዩ ድጋፍ ያደርጋል፤

፱/ ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ልማት ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፤

፲/ በሕግ መሠረት ውሎችንና ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ይፈራረማል፤

## SUB-SECTION TWO

## POWERS AND DUTIES OF MINISTRIES

### 19. Common Powers and Duties of Ministries

In accordance with this Proclamation and other laws each Ministry shall have the following power and duties within its jurisdiction:-

1/ Undertake research and studies; gather, synthesize, and disseminate information;

2/ Formulate study-based policies;

3/ Initiate Federal laws, and implement the same;

4/ Adopt Directives to fulfill its duties and responsibilities given by law;

5/ Work, by creating the necessary coordination with other Ministries and organs, to implement policies and strategies;

6/ Prepare plans and budgets, and implement the same upon approval;

7/ Undertake capacity building activities; implement and cause the implementation of reform and good governance activities; ensure the effectiveness of the same;

8/ Provide, as necessary, support and advice to Regions; provide special support to Regions or areas in need of special support;

9/ Provide appropriate support for the development of pastoral and semi-pastoral areas;

10/ Enter into contracts and international agreements in accordance with law;

https://chilot.me



፲፩/ የሚያዘጋጃቸው ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ሕጎች፣ የልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የሴቶችን፣ የሕፃናት፣ የወጣቶችን፣ አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያንን ጥቅም የሚያስጠብቅ መሆኑን ያረጋግጣል፤ የአካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን፣ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ተጋላጭ የኅብረተሰብ ክፍሎች የእኩል እድል ተጠቃሚና ሙሉ ተሳታፊ የሚሆኑበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

፲፪/ ስለሥራው ክንዋኔ በየወቅቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት እና ለሚመለከታቸው ሌሎች አካላት ሪፖርት ያቀርባል፤

፲፫/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለሌላ የፌደራል ወይም የክልል አካል በውክልና ሊሰጥ ይችላል፤

## ፳. ግብርና ሚኒስቴር

፩/ የግብርና ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ) የግብርና እና የደን ልማትን እና ተወዳዳሪነትን በቀጣይነት የሚያረጋግጡ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣ ፕሮግራሞችን እና የሕግ ማዕቀፎችን ይቀርጻል፣ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

11/ Ensure that the policies, strategies, laws, development programs and projects it formulates benefit women, children, youth, persons with disability and elderly; facilitate conducive conditions to persons with disabilities, the elderly, and segments of society vulnerable to social and economic problems for full participation and benefit from equal opportunities;

12/ Submit periodic performance reports to the Prime Minister, Council of Ministers, and other concerned bodies;

13/ Where necessary, delegate part of its powers and duties to other Federal or Regional Organ.

## 20. Ministry of Agriculture

1/ The Ministry of Agriculture shall have the following powers and duties:

a) formulate policies, strategies, programs and legal framework which ensures the sustainability of agriculture and forest development and its competitiveness; implement the same upon approval by the concerned organs;

https://chilot.me


ለ) በግብርና ዘርፍ ልማት የግል ዘርፉን ተሳትፎና ሚና ለማሳደግ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ለአፈጻጸሙ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፣ የሥጋ እና የወተት ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በዘርፉ የሚሰማሩ የግል ባለሀብቶች እና የህብረት ሥራ ማህበራት አስፈላጊውን ድጋፍ የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ ውጤታማነቱን ያረጋግጣል፤

ሐ) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ለአርሶ አደሮች፣ ለአርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች እና በግብርና ሥራ ላይ ለተሰማሩ የግል ዘርፍ ተዋንያን ተደራሽ የሆነ የግብርናና ገጠር ፋይናንስ ሥርዓት እንዲዘረጋ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል፣ የግብርና የህብረት ሥራ ማህበራት እንዲስፋፉና እንዲጠናከሩ ያደርጋል፤

መ) የሰብል፣ የእንስሳትና የዓሳ ምርት ምርታማነትን ለማሳደግ፣ የምርት ተወዳዳሪነትን ለማረጋገጥ የግብርና ኤክስቴንሽን ምክር አገልግሎት፣ የቴክኖሎጂ እና አመራረት ስልቶች አቅርቦት እንዲስፋፋና አጠቃቀሙም እንዲያድግ ያደርጋል፣ ውጤታማነታቸውን ያረጋግጣል፤

b) establish a system which enables to promote the participation and role of the private sector in agricultural sector development; create conducive conditions for the implementation of the same; facilitate the provision of the necessary support for private investors and cooperatives engaged in the sector in order to raise meat and milk production and productivity, ensure its effectiveness;

c) create, in coordination with concerned organs, conducive condition for the establishment of rural financial system accessible to farmers, pastoralists, and semi-pastoralists and to private sector actors engaged in agricultural activities; follow up its implementation; cause the expansion and strengthening of agricultural cooperatives;

d) cause the expansion and utilization of agricultural extension advisory service, supply of technology and techniques of production in order to promote production and productivity of crops, livestock and fishery; ensure the effectiveness of the same;

https://chilot.me


ሠ) በሰብል ምርት፣ በእንስሳትና ዓሳ እና የተፈጥሮ ሀብት ልማት ግብዓቶች ፍላጎት፣ አቅርቦት፣ ሥርጭትና ግብይት ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣ ውጤታማነቱን ያረጋግጣል፤

ረ) የእፅዋት፣ እንሰሳትና ዓሳ በሽታዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ በዚሁ ረገድ የሚደረጉ ጥናትና ምርምሮችን ይመራል ያስተባብራል፣

ሰ) የእፅዋትና እንስሳት ጤና አገልግሎትን ጥራትና ተደራሽነት ለማሻሻል የሚያስችሉ ሥርዓቶችንና መሠረተ ልማቶችን ይዘረጋል፣ እንደአስፈላጊነቱ ላብራቶሪዎችና ክሊኒኮች እንዲገነቡ ያደርጋል፣ አቅማቸውን ይገነባል፣ ውጤታማነታቸውን ያረጋግጣል፤

ሸ) የግብርና ቴክኖሎጂ፣ ግብዓት እና አገልግሎት ምዝገባና ቁጥጥር ይዘርጋል፣ የምርት ጥራት፣ ጤናና ደህንነት ቁጥጥር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ወደ ሀገር በሚገቡትም ሆነ ከሀገር በሚወጡት የእፅዋት ቁጥጥር እና እንሰሳትና የእንሰሳት ተዋጽኦዎች ላይ የኳራንቲን ቁጥጥር ሥራን ያስተባብራል፤

ቀ) የከተማ ግብርናን ውጤታማ ለማድረግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ስልት ይነድፋል፣ የአተገባበር ሥርዓት ይዘረጋል፤

e) establish a system for demand, supply, distribution and marketing inputs for crop production, veterinary, fishery and natural resource development; follow up the implementation and effectiveness of the same;

f) establish a system which enable the prevention and control of plant, animal and fish diseases; lead and coordinate studies and researches with respect to the same;

g) establish a system and infrastructure that enable to improve the quality and accessibility of plant and veterinary health services; cause the construction of laboratories and clinics as may be necessary and build their capacity and monitor its effectiveness;

h) establish a system for registration and monitoring of agricultural technology, input and service; establish a system for monitoring quality, health and safety of production; coordinate monitoring activities on plants and quarantine of animals and animal products brought into and taken out of the country;

i) devise strategy, in collaboration with the concerned organs, in order to make urban farming effective and establish implementation mechanisms;

https://chilot.me



በ) የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ሥራዎች በአግባቡ መተግበራቸውን ያረጋግጣል፤ የእንስሳትና የዓሳ ምርትና ተዋጽኦ የጥራት ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎችን በምርምር በመለየት ወደ ገበያ የሚገቡበትን ሥርዓት ይመራል፣ ያስተባብራል፣ የእንስሳትና የዓሳ ምርትና ተዋጽኦ ምርቶች በሀገር ውስጥ እና በውጪ ገበያ የሚተዋወቁበትን ሥርዓት ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመተባበር ይዘረጋል፤

ተ) ለእንስሳትና ዓሳ ምርትና ተዋጽኦ ልማት አስፈላጊ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን የማደራጀትና እንደአስፈላጊነቱ ለተጠቃሚዎች የማስተዋወቅ ሥራ ያስተባብራል፤

ቸ) ለገጠር መሬት አስተዳደርና ለተፈጥሮ ግጦሽ መሬት ዘላቂ የአጠቃቀም ሥርዓት መዘርጋቱን ይከታተላል፣ ድጋፍ ይሰጣል፣ ሀገር አቀፍ መረጃ ያደራጃል፤

ኀ) በአርብቶ አደርና በከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች በገበያ የሚመራ የእንስሳት ሀብት ልማት፣ ውሃን ማዕከል ያደረገ የሰብልና የእንስሳት መኖ ልማት፣ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት እና የግጦሽ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ልማት አጠቃቀም ሥርዓት እንዲዘረጋ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ይሠራል፤

j) ensure the proper implementation of animal genetic improvement; lead and coordinate system for identification of technologies that enable to maintain the quality of animal and fish production and their products through research and making the same enter the market; establish, in collaboration with the concerned institution, a system for the introduction of livestock and fishery products to domestic and foreign markets;

k) coordinate the compilation of technologies necessary for livestock and fishery products development and the introduction of the same to users as may be necessary;

l) follow up and support the establishment of a system for rural land management and sustainable utilization of natural grazing land; organize a national data base;

m) cause, in coordination with the concerned organs, the establishment of a system for market led veterinary resource development, water centered crops and animal feed development, vegetables and fruits development and utilization of grazing land and natural resource in pastoralist and semi pastoralist areas;

https://chilot.me



ነ) ለግብርና የሚውል ውሃን ከዝናብ፣ ከገጸ-ምድር እና ከከርሰ-ምድር ምንጮች በማቀናጀት የውሃ ማቆር ሥራዎች፣ የወንዝ ጠለፋ፣ የምንጭ ማጐልበትና የውሃ መሣቢያ ሞተሮች አጠቃቀም የሚጠናከርበትን ሥርዓት ይዘረጋል፣ ውጤታማነቱን ይከታተላል፤ የአርሶ አደሩን እና አርብቶ አደሩን የውሃ አጠቃቀም ክህሎት የበለጠ ለማሳዳግ የድጋፍ እና ማበረታቻ ሥርዓት ይዘረጋል፣ ውጤታማነቱን ያረጋግጣል፤

ኘ) የተፋሰስ፣ የአፈርና ውሃ አያያዝና አጠቃቀምን፣ የውሃ ተፋሰስንና የእርጥበታማ መሬቶች አያያዝ ፕሮግራሞች እና ፕሮጀክቶች ተነድፈው ተግባራዊ የሚሆኑበትን ሥርዓት ይዘረጋል፣ እንዲስፋፉ ያደርጋል፣ ውጤታማነታቸውን ይከታተላል፤

አ) የተፈጥሮ ሀብትን ለመጠበቅና በዘላቂነት ለመጠቀም የተፈጥሮ ሀብት መመናመን መንስዔዎችን ይለያል፣ የመከላከያ ስልቶች ተነድፈው ተግባራዊ የሚሆኑበትን ሥርዓት ይዘረጋል፣ ውጤታማነታቸውን ይከታተላል፤ የአፈር መሸርሸር መንስዔዎች ልየታ ሥራን፣ የመከላከያ ስልቶች ተነድፈው ተግባራዊ የሚሆኑበትን ሥርዓት ፣ የአፈር ለምነት የሚሻሻልበትን፣ የአፈር ጤንነት የሚጠቅበትን እና ሀገራዊ የአፈር መረጃ ሥርዓትና የአፈር ምርምር ተግባር የሚከናወንበትን ስልት የመንደፍ ሥራን ያስተባብራል፤

n) establish a system for the strengthening of water harvesting, diversion of water, development of ground water resource, utilization of water pumps activities by integrating water used for farming with rain, surface and ground water; establish a support and incentive system to upgrade the water utilization skills of farmers and pastoralists; ensure its effectiveness;

o) establish a system for the formulation and implementation of programs and projects for utilization of river basin, soil and water; conservation of river basin and wet lands and cause the expansion of the same and follow up its effectiveness;

p) identify the causes for the extinction of natural resource in order to conserve and sustainably utilize it and establish a system for formulation and implementation of prevention strategies and follow up its implementation; coordinate the formulation and implementation of strategies for identification of causes of soil erosion and prevention of the same, improvement of soil fertility; maintenance of soil health and cause the coordination of devising strategy national soil database and soil research activities;

https://chilot.me



ከ) የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋ በግብርና ልማት ላይ የሚያስከትለውን ተጽዕኖ ለመተንበይ የሚያስችል አቅም ይገነባል፣ የአደጋ ተጋላጭነትን ለመቀነስና የመቋቋም አቅምን ለማጠናከር የዕለት ደራሽ ድጋፍ እና የምግብ ዋስትና የሚረጋገጥበትን ሥርዓት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ይዘረጋል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣ በገጠር የልማታዊ ሴፍትኔት ፕሮግራሞችን ያስተባብራል፤

ኸ) ከመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር፣ የሰብልና እንስሳት ምርትና ምርታማነት እንዲያድግ በጥናት ግኝት ላይ የተመሠረተ ለቆላማ አካባቢዎች ግብርና ሥራዎች የሚውል የውሃ እና የመሬት አጠቃቀም እና የመስኖ ኤክስቴንሽን ሥርዓት ይቀይሳል፤ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤

ወ) የግብርና ልማት በገበያ እንዲመራና ዘመናዊ አመራረት እንዲጎለብት የቴክኒክ ድጋፎችን ይሰጣል፣ የገበያ ትስስር እንዲፈጠር ያደርጋል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በገበያ የሚቀርብ ማናቸውንም የሰብል ምርት፣ እንስሳትና ዓሳ ምርትና ተዋጽኦ የጥራት ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

q) build capacity which enables to predict the impact of natural and man-made disasters on agricultural development; establish, in collaboration of the concerned organs, a system for mitigation of vulnerability and resilience capacity of the same, ensuring emergency relief support and food security; implement the same; coordinate rural productive safety net program;

r) design, in collaboration with Ministry of Irrigation and Lowland, a system for utilization of water and land for the growth of production and productivity of crops and livestock to be used for agricultural activities in lowland areas based on research findings and follow up its implementation;

s) provide technical assistant in order to introduce market led agricultural development and to promote modern farming; cause the creation of market linkage; establish a system which enable to maintain quality standard of any crops, livestock or livestock and fishery product to be supplied to the market in collaboration with the concerned organs; and follow up its implementation;

https://chilot.me



ዐ) ከሚመለካታቸው አካላት ጋር ቅንጅት በመፍጠር የግብርና ኢንቨስትመንትን የሚመለከቱ ሥራዎች በአግባቡ መደራጀታቸውን ያረጋግጣል፤ ሰፋፊ የግብርና ኢንቨስትመንት አማራጮችንና እምቅ አቅሞችን ይለያል የኢንቨስትመንት ሥራዎች የሚስፋፉበትን ስልት ይቀይሳል፣ በዘርፍ ለተሰማሩ ባለሀብቶች የሚያስፈልጋቸውን ድጋፍ እንዲያገኙ ያደርጋል፣ ውጤታማነታቸውን ያረጋግጣል፤

ዘ) የግብርና ምርት ደህንነቱ የተጠበቀ፣ በንጥረ-ነገር ይዘቱ የበለፀገ የተሰባጠረና ጤናማነቱ የተጠበቀ የአመራረት ሥርዓት መኖሩን ያረጋግጣል፤

ዠ) የግብርናና የሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ትስስር ለማጠናከር ከሚመለከታቸው የፌደራልና የክልል አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል፣ ለዘርፉ አሳታፊና ዘላቂ መዋቅራዊ ለውጥ የሚመጣበትን ስልት ይነድፋል፣ ተግባራዊ የሚሆኑበትን ሥርዓት ይዘረጋል፤

የ) የግብርና ምርምር ሥራዎች የዘርፉን ችግር የሚፈቱ መሆናቸውን እና እንደአስፈላጊነቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መሰራታቸውን ያረጋግጣል፣ ያስተባብራል፤

ደ) የቡናና የሻይ ልማት እና ግብይት ሥራዎች በአግባቡ መተግበራቸውን ይከታተላል፣ ያስተባብራል፤

t) ensure that activities related agricultural investment are properly organized in coordination with the concerned organ; identify large agricultural investment opportunities and potentials and devise a strategy for the expansion of large-scale agricultural investment; cause the provision of support for investors engaged in the sector;

u) ensure that the system of production of agricultural products are safe and rich in nutrition, diversified and healthy;

v) work in coordination with the concerned Federal and Regional organs in order to strengthen the linkage between agriculture and other economic sectors; devise strategy to bring about inclusive and sustainable structural change; establish a system for its implementation;

w) ensure that agricultural research activities are problem solving and ensure that they are conducted in coordination with the concerned organs and coordinate the same;

x) follow up and coordinate the proper implementation of coffee and tea development and marketing activities;

https://chilot.me



ያ) የሀገሪቱን የብዝሀ ሕይወት ሀብቶች በአግባቡ በማንበር፣ በዘላቂነት ጥቅም ላይ እንዲውል በማደረግና ፍትሐዊ የጥቅም ተጋሪነትን በማረጋገጥ ሀገሪቱንና ሕብረተሰቡ ከብዝሀ ሕይወትና ተያያዥ ነባር የማህበረሰብ እውቀት እንዲሁም ከሥርዓተ ምኅዳር አገልግሎቶች የሚያገኙት ጥቅም በዘላቂነት እንዲያድግ ድጋፍ ያደርጋል፤

ገ) በደን ልማት፣ ጥበቃ እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፷፭/፪ሺ፲ ላይ ለአካባቢ፣ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባራትን በሥራ ላይ ያውላል፡፡

፪/ በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች ለግብርና ሚኒስቴር የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው ግብርና ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

**፳፩. <u>የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር</u>**

፩/ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

ሀ) የኢንዱስትሪ በተለይም የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማትንና ተወዳዳሪነትን በቀጣይነት የሚያረጋግጡ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣ ፕሮግራሞችን እና ሕጎችን ያመነጫል፣ ለአፈጻጸሙ ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርሀ-ግብር ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

y) provide support for the sustainable upgrading of the benefit that the country and the community obtains by ensuring the proper preservation of biodiversity resources and related community knowledge and eco system services, through sustainable use and equitable utilization of benefit sharing of the same;

z) implement the powers and duties entrusted to Ministry of Environment, Forest and Climate Change under Forest Development, Conservation and Utilization Proclamation No. 1065/2018.

2/ Powers and duties entrusted to the Ministry of Agriculture under other laws that are currently in force are hereby vested in the Ministry of Agriculture established under this Proclamation.

**21. <u>Ministry of Industry</u>**

1/ The Ministry of Industry shall have the following powers and duties:

a) formulate policies, strategies, programs and legal framework that ensure the development and competitiveness of the industry in particular the development of the manufacturing industry in a sustainable manner; prepare detail program compatible with the national development plan and implement the same upon approval;

https://chilot.me



ለ) በኢንዱስትሪ በተለይም በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ የግል ዘርፉን ተሳትፎና ሚና ለማሳደግ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ለአፈጻጸሙ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፤

ሐ) በኢንዱስትሪ በተለይም ማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ልማት ትኩረት የሚሠጣቸውን ጨርቃ ጨርቅ፣ ቆዳ እና የምግብና መጠጥ ኢንዱስትሪዎችና የመሳሰሉት ንዑስ ዘርፎች ካላቸው አንጻራዊ ጠቀሜታና እምቅ አቅም አኳያ ይለያል፤ ለአፈጻጸሙ ዝርዝር ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ መርሀ-ግብር ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

መ) በዘርፉ ምርምርና ጥናት የሚያካሂዱ አካላትን አስፈላጊውን ድጋፍ በማድረግ የኢንዱስትሪዎችን፣ የኢንቨስትመንት እና የማኑፋክቸሪንግ አቅምና ተወዳዳሪነትን እንዲያድግ ያደርጋል፤

ሠ) በኢንቨስትመንት ሕግ መሠረት የሀገር ውስጥ እና የውጭ ባለሃብቶች በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ኢንቨስትመንት የሚሳተፉበትን ሁኔታዎች ያመቻቻል፤ በሥሩ ያሉ ተጠሪ ተቋማት በዋናነት ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ድጋፍ እንዲሰጡ ለማድረግ ተገቢውን ሥርዓት ይዘረጋል፣ ያስፈጽማል፤

b) create an enabling system for enhanced participation and role of the private sector in the industry in particular in the manufacturing industry; create conducive condition for the implementation of the same;

c) identify sub-sectors that require special attention in the industry in particular in the manufacturing sector such as textile, leather, food and beverages industries from comparative advantage and potential perspective; prepare detail program compatible with the national development plan and implement the same upon approval;

d) cause the building of capacity and enhancement of competitiveness of industries, investment and manufacturing industries by providing the necessary support for researchers in the sector;

e) create conducive conditions for the participation of domestic and foreign investors in the investment of manufacturing industry sector in accordance with the investment laws; establish a system to enable the institutions accountable to it to support mainly domestic investors and implement the same;

https://chilot.me



ረ) የኢንዱስትሪ በተለይም የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ልማትን ለማሳደግ የሚያስችሉ ተግባራትን፣ የምርጥ ተሞክሮ መቀመር፣ እና አጠቃላይ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት አቅም ግንባታ ሥራዎችን ይሰራል፤

ሰ) የኢንዱስትሪ በተለይም የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ልማትና ምርታማነትን ለማሳደግ ኢንዱስትሪዎች የኤክስቴሽን አገልግሎት፣ የቴክኖሎጂ፣ የግብዓትና የግብይት እንዲሁም በአመራረት ረገድ ድጋፍ እንዲያገኙ ያደርጋል፤ ውጤታማነታቸውንም ያረጋግጣል፤

ሸ) የኢንዱስትሪ በተለይም የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ምርቶች የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ፣ በዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የአቅም ግንባታ፣ የምርምርና ስርጸት ሥራዎች እንዲከናወኑ ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

ቀ) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ለኢንዱስትሪ በተለይም ለማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ አስፈላጊ የሆነው የሰው ኃይል ፍላጎት እና አስተማማኝ ግብዓት ለማሟላት የሚቻልበትን ስልት ይቀይሳል፤ ከሚመለከተው ዘርፍና አካላት ጋር በመሥራት የኢንዱስትሪ ግብዓት አቅርቦት ትስስር ሥርዓት እንዲዘረጋ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፤

f) perform activities that enhance the industry in particular the development of the manufacturing industry sector; expedite the acquisition of best practice and perform general capacity building activities in the manufacturing industry;

g) cause the provision of assistance including industrial extension services, technology, inputs, marketing and manufacturing methods and thereby ensure growth and productivity of the industry in particular in the manufacturing sector and monitor the effectiveness thereof;

h) establish a system of capacity building, research and inculcation to maintain quality standards and competitiveness of industrial in particular manufacturing industrial products in international markets; oversee implementation of the same;

i) devise, in collaboration with the concerned organs, mechanisms to meet human resources needs and sustainable input provisions required in the industry sector in particular in manufacturing industrial sector; work with the concerned sector and bodies to create conditions necessary for the establishment of a system for industrial input provision linkages and implement the same;

https://chilot.me



በ) ለዘርፉ እድገት ከሚመለከታቸው የፌደራልና የክልል አካላት ጋር በቅንጅት ይሠራል፣ ለዘርፉ አሳታፊና ዘላቂ መዋቅራዊ ለውጥ ስለሚመጣበት ሁኔታ ስልቶችን ይነድፋል፣ ተግባራዊ የሚሆኑበትን ሥርዓት ይዘረጋል፤

ተ) ለማዕድን ሚኒስቴር ከተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት ውጪ ያሉ ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታቸው ጉልህ የሆኑ የኢንዱስትሪ ገቢ ምርቶች በሀገር ውስጥ ምርቶች እንዲተኩ ድጋፍ ያደርጋል፤

ቸ) በአነስተኛ፣ በመካከለኛና በከፍተኛ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች መካከል የተቀናጀ ትስስር እንዲፈጠርና ስኬታማ ሽግግሮች እንዲከናወኑ የሚያስችሉ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች እና የአሠራር ሥርዓቶችን ይዘረጋል፤

ኀ) የአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን ውጤታማ እንዲሆኑ የማትጊያ ስልት ይቀይሳል፣ ድጋፍ ያደርጋል፤

ነ) የኢንዱስትሪ በተለይም የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች በአካባቢ ጥበቃ የተቀመጡ መስፈርቶችን እንዲያሟሉ ድጋፍ ያደርጋል፤

ኘ) የኢንዱስትሪ፣ የዘርፉ እና የሙያ ማህበራት እንዲቋቋሙ ያበረታታል፣ የተቋቋሙትንም እንዲበረታቱ ያደርጋል፡፡

፪/ በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ተሰጥተው የነበሩ ኢንዱስትሪን የሚመለከቱ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

j) work in collaboration with concerned Federal and Regional bodies to promote the industry sector; devise mechanism to bring inclusive and sustainable structural change in the sector and establish a system for implementation of the same;

k) support the substitution of import goods, other than those entrusted to the Ministry of Mines, having strategic importance with domestic products;

l) establish working mechanism and formulate policy and strategy that enable to create linkage and effective transformation between small, medium and large-scale industries;

m) devise mechanism for providing incentives in order to make small and medium enterprise effective and provide support for the same;

n) provide support to industry, in particular. to manufacturing industry to ensure compliance with environmental protection requirements;

o) encourage the establishment of industrial, sectorial and professional associations, and strengthen those already established;

2/ The powers and duties entrusted to the Ministry of Trade and Industry under other laws that are currently in force with respect to industry are hereby vested in the Ministry of Industry established by this Proclamation.

https://chilot.me


**፳፪. ንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር**

፩/ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

ሀ) የሀገር ውስጥና የውጭ ንግድን የሚመለከቱ ቀጣናዊ በተለይም ከጎረቤት ሀገራት ጋር የሚኖር የንግድና ኢኮኖሚያዊ ትስስርን በቀጣይነት የሚያረጋግጡ፣ ሀገራዊ የጥራት መሠረተ ልማቶችን የሚመለከቱ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ሕጎችን ያመነጫል፣ ለአፈጻጸሙ ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርሀ-ግብር ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

ለ) የሀገር ውስጥ ንግድ እንዲስፋፋና እንዲዘምን፣ ሕጋዊ አሠራር እንዲሰፍን ተገቢነት ያላቸውን እርምጃዎች ይወስዳል፤ በክልሎች መካከል የሚደረግን የንግድ ግንኙነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤

ሐ) የሀገሪቱ የወጪ ንግድ የሚስፋፋበትንና የሚጠናከርበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

መ) የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ምርቶቻቸውን ለውጭ ገበያ እንዲያቀርቡ ከሌሎች ተቋማት ጋር በመቀናጀት አስፈላጊውን ድጋፍ የሚሰጥበትን ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤

ሠ) አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የውጭ ንግድ ግንኙነቶችን ይመሠርታል፣ የንግድ ስምምነቶችን በሕግ መሠረት ይፈራረማል፣ ሲጸድቅም ያስፈጽማል፤

**22. The Ministry of Trade and Regional Integration**

1/ The Ministry of Trade and Regional Integration shall have the following powers and duties:

a) initiate policies, strategies and laws with respect to foreign and domestic trade in particular, regional trade and economic integration with neighboring countries and national quality assurance infrastructure; prepare detailed program compatible with national development plan for their implementation and implement the same upon approval;

b) take appropriate measures to expand and modernize domestic trade and maintain lawful trade practices; lead and oversee trade relations between regions;

c) create conducive conditions for the expansion and promotion of the country's export trade;

d) establish system, in collaboration with other organs, for the provision of support to domestic investors in exporting their products to overseas markets; and implement the same;

e) in collaboration with relevant organs, establish foreign trade relations, sign trade agreements in accordance with the law and implement the same upon approval;

https://chilot.me


ረ) የወጪና ገቢ ንግድ ዕቃዎችን ጥራት ይቆጣጠራል፣ ተፈላጊውን የደረጃ መሥፈርት የማያሟሉ የንግድ ዕቃዎች ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገቡ ወይም ከሀገር እንዳይወጡ ይቆጣጠራል፤

ሰ) የወጪና ገቢ ዕቃዎች በትክክለኛ ዋጋ ስለመሸጣቸው ወይም ስለመገዛታቸው ለማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ክትትል ያደርጋል፤

ሸ) ቀላል፣ ወጪ ቆጣቢና በቴክኖሎጂ የተደገፈ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት ሥርዓት ይዘረጋል፤

ቀ) የዋጋ ቁጥጥር ሊደረግባቸው የሚገቡ መሠረታዊ የንግድ ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን ዋጋ እያጠና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፤

በ) የንግድና የዘርፍ ማህበራት፣ የሸማቾች ማህበራት እንዲቋቋሙ ያበረታታል፣ የተቋቋሙትንም እንዲጠናከሩ ያደርጋል፤

ተ) የሀገሪቱን ሕጋዊ ሥነ-ልክና ተስማሚነት ሥርዓት ለመተግበር እንዲቻል አስፈጻሚ አካላትን ያስተባብራል፤

f) control the qualities of export and import goods; prohibit the importation or exportation of goods that do not conform with the required standards;

g) establish system to ascertain that export or import goods are traded or bought at appropriate prices; follow up the same in collaboration with concerned organs;

h) provide simple, cost effective and technology supported commercial registration and business licensing services;

i) undertake and submit to the Council of Ministers studies relating to prices of basic commodities and services that require price control; oversee implementation of the same upon approval;

j) encourage the establishment of chambers of commerce and sectorial associations, consumers' associations, and strengthen those which are already operational;

k) establish the legal metrological system of the country, oversee its enforcement and coordinate the concerned executive organs;

https://chilot.me



ቸ) አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ ያላቸው የንግድ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የደረጃውን መስፈርት ማሟላታቸውን ይቆጣጠራል፣ በሌሎች አስፈጻሚ መሥሪያ ቤቶች የሚሠራባቸው አስገዳጅ ደረጃዎች በተቀናጀ መልኩ እንዲተገበሩ ያደርጋል፤

ኀ) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ስትራቴጂካዊ ትኩረት በሚሰጣቸው ዘርፎች የሀገሪቱን ምርቶች ለውጭ ገበያ በማቅረብ ረገድ የታቀደውን እድገት ለማምጣት የሚያስፈልጉ ጥናትና ምርምሮች ያካሂዳል፣ ይተገብራል፤

ነ) አግባብ ባላቸው ሕጎች መሠረት ንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎቶችን ይሰጣል፣ የተሰጡ የንግድ ፈቃዶች ለተሰጠባቸው ዓላማ መዋላቸውን ይቆጣጠራል፤

ኘ) የንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ ሥራን ይሠራል፤

አ) በአዋጅ ቁጥር ፭፻፶፩/፲፱፻፺፱ ለኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን የተሰጡ ከዳኝነት ችሎት ሥራ ውጪ ያሉ ተግባርና ኃላፊነቶችን በሥራ ላይ ያውላል፤

ከ) በንግድ ውድድር እና ሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር ፰፻፲፫/፪ሺ፮ ለንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን ተሰጥተው የነበሩ ከዳኝነት ችሎት ሥራ ውጪ ያሉ ተግባርና ኃላፊነቶችን በሥራ ላይ ያውላል፡፡

l) control the compliance of goods with the requirements of mandatory Ethiopian standards, and take measure against those found to be below the standards set for them; cause the coordinated enforcement of standards applied by other enforcement bodies;

m) conduct studies and researches to facilitate the realization of plans that enhance export industries having strategic importance; and implement the same in collaboration with the relevant organs;

n) provide commercial registration and business licensing services in accordance with the relevant laws; ensures the use of such business licenses for the authorized purposes;

o) perform trade competition and consumer protection functions;

p) implement powers and duties, other than adjudication, entrusted to Ethiopian Commodity Exchange Authority under Ethiopian Commodity Exchange Authority Proclamation No. 551/2007;

q) implement powers and duties, other than adjudication, entrusted to Trade Competition and Consumer Protection Authority under Trade Competition and Consumer Protection Authority Proclamation No. 813/ 2013;

https://chilot.me


፪/ በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች ለንግድ ውድድሮችና ሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን፣ ለኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን እና ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የተሰጡ ንግድን የሚመለከቱ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

፳፫. **የማዕድን ሚኒስቴር**

፩/ የማዕድን ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

ሀ) የማዕድን፣ የጂኦተርማል፣ ነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ልማትን የሚመለከቱ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና የሕግ ማዕቀፍ ያመነጫል፣ ለአፈጻጸሙ ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርሀ-ግብር ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

ለ) የማዕድን፣ ነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ፍለጋንና የሥነ-ምድር መረጃዎች ማደራጀትን ሥራን ያስተባብራ፣ መረጃዎችን ለኢንቨስትመንትና ለልማት ተደራሽ ያደርጋል፤

ሐ) የማዕድን፣ ነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ልማት ሥራዎችን ለማፋጠን የሚውሉ የቤተ-ሙከራና የማዕድን ጥራት ማረጋገጫ ማዕከላትን እንዲሁም የምርምርና የማሰልጠኛ ተቋማትን እንደአስፈላጊነቱ ያደራጃል፤

መ) በማዕድን፣ ነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ልማት መስክ የሚፈለገውን የሰው ሀብት ለማልማት ከትምህርት ተቋማትና ከሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ይሠራል፤

2/ The powers and duties entrusted to Ministry of Trade and Industry, Trade Competition and Consumer Protection Authority and Ethiopian Commodity Exchange Authority under other laws that are currently in force with respect to trade are hereby vested in the Ministry of Trade and Regional Integration established by this Proclamation.

23. **Ministry of Mines**

1/ The Ministry of Mines shall have the following powers and duties:

a) initiate policies, strategies and laws pertaining to the development of minerals, geothermal, petroleum and natural gas; prepare detail program compatible with national development plan; implement the same upon approval;

b) coordinate the activities of organizing minerals, petroleum and natural gases exploration and geophysical data; cause its accessibility to investment and development thereof;

c) organize, as may be necessary, laboratories and minerals quality assurance centers, and research and training centers that accelerate the development of minerals, petroleum and natural gases;

d) work in collaboration with educational institutions and other concerned organs to produce trained manpower required in the development of minerals, petroleum and natural gases;

https://chilot.me



ሠ) የማዕድን፣ የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ኢንቨስትመንትና ልማት የግል ዘርፉ ተሳትፎና ሚናን ለማሳደግ የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፤

ረ) የማዕድን፣ የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ምርት ፍለጋን በበላይነት ይመራል፣ ምርቱን ወደ ገበያ ለማሸጋገር የሚያስችል ዘመናዊ አሠራሮችን ይዘረጋል፤

ሰ) ተጨማሪ እሴት ያላቸውን የማዕድን፣ ነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ምርቶች ላይ የሚሰማሩ የውጭ እና የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን የኢንቨስትመንት እና ማምረት አቅም ለማጎልበት የምርምር፣ የክህሎት ልማት እና የቴክኖሎጂ ሽግግር ሥራዎችን ያበረታታል፣ ይደግፋል፤

ሸ) በማዕድን፣ በጂኦተርማል፣ በነዳጅና በተፈጥሮ ጋዝ ፍለጋና ልማት ለሚሰማሩ፣ የማዕድን ግብዓቶችን በዋነኛነት ተጠቅሞ የኢንዱስትሪ ውጤቶችን በማምረት ሥራዎች ለሚሠማሩ የሀገር ውስጥ እና የውጭ ባለሀብቶች እና ኩባንያዎች አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት ፈቃድ ይሰጣል፣ የክፍያ ግዴታቸውን መወጣታቸውን ይከታተላል፣ ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፤ ያስተዳድራል፤

e) devise a system to promote the participation and role of the private sector in investment and development of minerals, petroleum and natural gases; create conducive conditions for the same;

f) oversee the exploration of minerals, petroleum and natural gas; set advanced system for the supply of products to markets;

g) promote and support research, skill development and technology transfer with a view to developing investment and production capacity of domestic and foreign investors engaged in the production of value-added minerals, petroleum and natural gas products;

h) issue licenses to domestic and foreign investors or companies engaged in exploration and development of minerals, geothermal, petroleum and natural gas and to those engaged in industrial production by mainly using mineral inputs; ensure that they have discharged their payment obligation, follow up, support and administer the same;

https://chilot.me


ቀ) ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታቸው ጉልህ የሆኑ እና ከውጪ የሚገቡ ማዕድንና የማዕድን ውጤቶች የሆኑ የሲሚንቶና ድንጋይ ከሰል፣ ሴራሚክ፣ ማርብልና ግራናይት፣ የብረት ማዕድን፣ የተለያዩ ኮንስትራክሽን ግብዓቶች፣ የፖታሽና የማዳበሪያ እና፣ የፔትሮሊየም ልማት ውጤቶች በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፣ የምርመራና የምርት ፈቃድም ይሰጣል፣ ከፍለጋ እስከ ምርት ያለውን የምርት ሰንሰለት ውጤታማ እንዲሆን ሙሉ ድጋፍ ያደርጋል፤

በ) የማዕድን ምርቶች የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ፣ በዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የአቅም ግንባታ፣ የምርምርና ልማት ሥራዎች እንዲከናወኑ ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

ተ) ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመተባበር በባህላዊ መንገድ የሚመረቱ ማዕድናት ቴክኖሎጂን በመጠቀም ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያስችል ውጤታማና ቀልጣፋ የአሠራር ሥርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል፤

ቸ) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በባህላዊና በአነስተኛ ደረጃ የሚመረቱ የከበሩና ጌጣጌጥ ማዕድናት ምርትና ግብይት ሕጋዊ መስመር እንዲይዝ አስፈላጊ ሥርዓትና መሠረተ ልማቶችን ይዘረጋል፤

i) create a conducive environment for the domestic production of imported and strategically beneficial mineral and mineral products such as cement, coal, ceramic, marble and granite, iron ore, various construction inputs, potash and fertilizers petroleum development outputs; issue exploration and production permit to the same; provide support the effectiveness of exploration to production chain of the same;

j) devise a system for capacity building, research and development works in order to ensure the quality and international competitiveness of mineral products; follow up implementation of the same;

k) establish, in collaboration with concerned organs, effective and efficient system that enhances the production and productivity of traditionally produced minerals by using technology;

l) establish the necessary system and infrastructure in collaboration with the concerned organs to legalize the production and marketing in precious and ornamental minerals produced in traditional and small scales;

https://chilot.me


ጎ) የማዕድንና ነዳጅ ሥራዎች በሚከናወንበት አካባቢ የአካባቢ ማህበረሰብን ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጡ እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፤የሕግ ማዕቀፍ ያመነጫል፣ በሚመለከተው አካል ሲጸድቁም በአግባቡ መፈጸማቸውን ያረጋግጣል፣ በአካባቢ ጥበቃ የተቀመጡ መስፈርቶችን መሟላታቸውን ይከታተላል፤

፪/ በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች ለማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው ማዕድን ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

**፳፬. <u>የቱሪዝም ሚኒስቴር</u>**

፩/ የቱሪዝም ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

ሀ) የቱሪዝም ልማትና ተወዳዳሪነትን በቀጣይነት የሚያረጋግጡ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና የሕግ ማዕቀፎችን ያመነጫል፣ ለአፈጻጸሙ ከሀገራዊ የልማት እቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርሀ-ግብር ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

ለ) በቱሪዝም ዘርፍ ልማት የግል ዘርፉን ተሳትፎና ሚናን ለማሳደግ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ለአፈጻጸሙ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፣

m) create conditions to benefit local communities in areas where mining operations and explorations of petroleum are pursued; initiate legal frameworks and ensure its implementation upon approval by the concerned organ; follow up the fulfillment of the requirements set for environmental protection;

2/ The powers and duties entrusted to the Ministry of Mines and Petroleum under other laws that are currently in force are hereby vested in the Ministry of Mines established by this Proclamation.

**24. <u>Ministry of Tourism</u>**

1/ The Ministry of Tourism shall have the following powers and duties:

a) initiate policies, strategies and laws which ensure sustainable of tourism development and its competitiveness; prepare detail program compatible with the national development plan for their implementation; and implement the same upon approval by the concerned organ;

b) establish a system which enable to promote the participation and roles of the private sector in tourism development; create conducive condition for its implementation;

https://chilot.me



ሐ) የሀገሪቱን የቱሪዝም እና የኢኮ-ቱሪዝም አለኝታዎችና መስህቦች በአግባቡ እንዲለዩና እንዲታወቁ ያደርጋል፣ ለቱሪዝም አመቺ ሆነው እንዲደራጁና እንዲለሙ ያደርጋል፤

መ) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ለቱሪዝም ጉብኝት እጅግ አስፈላጊ የሆኑ የቱሪዝም መዳረሻዎችን መሠረተ ልማት ይዘረጋል፣ ተጨማሪ አዳዲስ መሠረተ ልማቶች እንዲገነቡ ያደርጋል፤

ሠ) አዳዲስ የቱሪዝም መስህቦች እንዲለሙ ያደርጋል፣ የልማት ክፍተት ባለባቸው ቦታዎች የቱሪዝም መዳረሻዎች ያለማል፤ ነባር የቱሪዝም መዳረሻዎች እንዲጎለብቱ እና የቱሪዝም ምርት እና አገልግሎት በዓይነትና በመጠን እንዲያድጉ በማድረግ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ያደርጋል፣ የግል ባለሀብቶችም በልማቱ እንዲሳተፉ ያበረታታል፤

ረ) የተለያዩ የቱሪዝም ባለድርሻ አካላት የሚያከናውኗቸውን የቱሪዝም ገበያ ፍለጋና ማስተዋወቅ፣ የገበያ ትስስር እና ብራንዲንግ ሥራዎችን በማቀናጀትና በመምራት የሀገሪቱን የቱሪዝም ሀብቶች፣ መስህቦችና መልካም ገፅታ በውጭ ሀገርና በሀገር ውስጥ በስፋት ያስተዋውቃል፤ አዳዲስ የቱሪዝም ገበያዎችን ይፈጥራል፣ የዘርፉን የገበያ ድርሻ እንዲያድግ ያደርጋል፤

c) cause the proper identification and introduction of the country's tourism and eco-tourism potential and tourism attraction and organize and develop them in a way that is conducive for tourism;

d) establish infrastructure of tourism destination which are very important for tourism visit in cooperation with the concerned organs; cause the construction of new infrastructures;

e) cause the development of new tourism attraction, develop tourism destinations of development gap, promote existing tourism destinations; cause the competitiveness of tourism service in terms of types and quantity; encourage private sectors to engage in tourism development;

f) coordinate the tourism market search and introduction conducted by various tourism stakeholders; introduce the country's tourism resources, attraction and image in foreign country and in Ethiopia by coordinating and leading the market linkage and branding activities; create new tourism markets; promote the sector market share;

https://chilot.me



ሰ) ዘርፉ በቴክኖሎጂ፣ በጥናትና ምርምር እንዲደገፍ እና ለሀገራዊ ኢኮኖሚ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ እንዲያድግ ያደርጋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

ሸ) የቱሪዝም መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያደራጃል፣ ያሰራጫል፤

ቀ) የሀገሪቱ የተፈጥሮ ቅርሶች እንዲጠኑ፣ እንዲጠበቁና ለቱሪዝም አመቺ ሆነው እንዲለሙና ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚደረጉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

በ) በፌደራል መንግስት እንዲተዳደሩ የተሰየሙ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች በአግባቡ እንዲጠበቁ፣ ለቱሪዝም አመቺ ሆነው እንዲለሙና እንዲመሩ የማደረግ ሥራን ያስተባብራል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ስትራቴጂዎች እና ፕሮግራሞች ይቀርጻል፣ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤

ተ) የሀገሪቱ የቱሪስት መስህቦች በዓለም አቀፍ ቅርስነት ለማስመዝገብ የሚያስችሉ ቅድመ ሁኔታዎችን በማሟላት የሚመዘገቡበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

ቸ) የሀገሪቱን የቱሪዝም መስህቦች፣ ምርትና አገልግሎቶች መለያ በመቅረጽና በየጊዜው በማሻሻል በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

ኀ) የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ደረጃዎች ይወስናል፣ ተፈጻሚነቱን ይቆጣጠራል፤

g) support the sector with technology, study and research and cause the promotion of the sector's contribution to the country's economy and follow up its implementation;

h) collect, compile and disseminate tourism information;

i) create conducive condition for the study, preservation of the country's natural heritage and its development and utilization as tourist attraction;

j) coordinate the conservation of wildlife areas designated to be administered by the federal government and development and management of such areas; formulate strategies and programs in cooperation with the concerned organs; follow up implementation of the same;

k) create conducive condition for the registration of the country's tourist attraction as an international heritage by fulfilling the preconditions for registration;

l) design tourism labels for identification of the country's tourism attraction, production and service and improve them from time to time and cause the implementation of the same;

m) determine the standard of tourist service providers and supervise its implementation;

https://chilot.me


ነ) ሥልጣኑ በግልጽ በሌላ አካል ካልተሰጠ በስተቀር ከአንድ በላይ በሆኑ ክልሎች ውስጥ አገልግሎት ለሚሰጡ ወይም ሕግ በሚፈቅደው አግባብ በውጭ ባለሀብቶች ለሚካሄዱ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፤

ኘ) ከቱሪዝም ተዋናዮች ጋር አጋርነትና ትብብር በመፍጠር ይሰራል፤

አ) የመንግሥትና በቱሪዝም ዘርፍ የተሰማሩ የግል ዘርፍ አካላትን ያስተባብራል፣ ከክልል የቱሪዝም አካላት ጋር በጋራ የሚሰራበትን ማዕቀፍ በማዘጋጀት በሥራ ላይ ያውላል፤ ጥራት ያለው የቱሪዝም አገልግሎትና የቱሪስቶችን ደህንነት ለማረጋገጥ ያሉትን ዘርፈ-ብዙ ጥረቶች ለማስተባበር በቱሪዝም ዙሪያ የጋራ መድረክ ይፈጥራል፤

ከ) ሥልጣንና ተግባራቱን ለማስፈጸም እንዲያስችለው የሚቋቋመውን የቱሪዝም ፈንድ ያስተዳድራል፤

ኸ) የግል ዘርፍ አካላትንና የቱሪዝም ዘርፍ ልማት የሚመለከታቸው የፌደራል እና የክልል መንግስት ተቋማትን ለማስተባበር የኢትዮጵያ ቱሪዝም ቦርድ በሕግ የሚደራጅበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

ወ) የቱሪዝም ዘርፍ መረጃ ሥርዓትን ይዘረጋል፤ ከፕላንና ልማት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የቱሪዝም ሳተላይት አካውንት በሀገራዊ የኢኮኖሚ አካውንት ሥርዓት ውስጥ ለማዋሃድ ሥርዓት ይዘረጋል፤

n) issue, unless such power is clearly given to other organ, license to investors who provide service in more than one region or, where the law so provides, to tourist service providers to be conducted by foreign investors; supervise the same;

o) work by creating partnership and cooperation with tourism actors;

p) coordinate government and private sector engaged in tourism sector; prepare and implement a framework to work in partnership with regional tourism organs; create a joint platform in connection with tourism to coordinate multifaceted efforts in order to ensure quality tourism service and safety of tourists;

q) administer tourism fund to be established to enable it to implement its power and duties;

r) create conducive condition for the establishment of Ethiopian Tourism Board by law to coordinate the private sector and federal and regional institutions concerned with tourism sector development;

s) establish information system of tourism sector; establish a system to integrate tourism satellite account with the country's economic account system in collaboration with the Ministry of Plan and Development.

https://chilot.me


፪/ በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች ለባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የተሰጡ ቱሪዝምን የሚመለከቱ እና ለቱሪዝም ኢትዮጵያ የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው ቱሪዝም ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

**፳፭. <u>የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር</u>**

፩/ የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

ሀ) የሥራ፣ የሥራ ስምሪትና ክህሎት፣ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ሕጎችን ያመነጫል፣ ለአፈጻጸሙ ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርሀ-ግብር ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

ለ) የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ከሀገሪቱ አጠቃላይ የልማት ፖሊሲና ከሥራ፣ ከሥራ ስምሪትና ክህሎት እድገት ጋር አብሮ ለማስኬድ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

ሐ) ከሚመለከታቸው የኢኮኖሚና ማህበራዊ ዘርፎች ጋር በመቀናጀት የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና የሥርዓት-ሥልጠና ማዕቀፍ ይቀርፃል፣ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤ በሚመለከተው አካል ለቴክኒክና ሙያ ተቋማት የወጡ ደረጃዎች መፈጸማቸውን ይከታተላል፤

2/ The powers and duties entrusted to Ministry of Culture and Tourism and Tourism Ethiopia under other laws that are currently in force with respect to Tourism are hereby vested in the Ministry of Tourism established by this Proclamation.

**25. <u>Ministry of Labor and Skills</u>**

1/ The Ministry of Labor and Skills shall have the following powers and duties:

a) initiate policies, strategies and laws with respect to labor, employment and skill; prepare detail program compatible with the national development plan and implement the same upon approval;

b) establish a system for technical and vocational training that are in line with the country's general development policy, labor, employment and skill development; follow up the implementation of the same;

c) formulate, in collaboration with concerned economic and social sectors, technical and vocational training curricula; implement the same upon approval; ensure the implementation of standard set for technical and vocational institutions;

https://chilot.me



መ) ከሚመለከታቸው የኢኮኖሚና ማህበራዊ ዘርፎች ጋር በማቀናጀት በቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማት እና በዘርፎቹ መካከል ለሥራ ገበያና ስምሪት እንቅስቃሴ የሚያግዝ ምቹ የእርስ በእርስ ትስስር እንዲፈጠር ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

ሠ) የሰው ኃይል ልማትን ለማፋጠንና የቴክኖሎጂ አጠቃቀምና ውጤታማነት ለማሻሻል የሚረዱ የማሰልጠኛ ማዕከሎችን ያቋቁማል፣ ይመራል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

ረ) ከሚመለካታቸው የኢኮኖሚና ማህበራዊ ዘርፎች ጋር በመቀናጀት ቀልጣፋና ፍትሐዊ የሥራ እድልና ስምሪት አገልግሎቶች ተደራሽነት እንዲስፋፋ ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

ሰ) የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ሕጎች በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

ሸ) ተቀማጭነታቸው ከአንድ ክልል በላይ የሆኑ ድርጅቶችን የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ይከታተላል፣ ድጋፍ ይሰጣል፤

ቀ) በሥራ ላይ የሚከሠቱ አደጋዎችና በሥራ ምክንያት የሚመጡ በሽታዎችን ለመከላከል የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፤ የሙያ ጤንነትና ደኅንነት ደረጃዎች ያወጣል፣ ሥራ ላይ መዋላቸውን ይቆጣጠራል፤

በ) የኢንዱስትሪ ሠላም ለማስጠበቅ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱንም ያረጋግጣል፤

d) create, in collaboration with the concerned economic and social sectors, conducive conditions for facilitating linkages which promote labor market and employment activity;

e) establish, manage and follow up implementation of training centers that enable to accelerate human resource development and utilization and effectiveness of technology;

f) establish, in collaboration with concerned economy and social sectors, a system for the expansion of efficient, accessible and equitable job opportunity and employment; follow up implementation of the same;

g) monitor and follow up the proper implementation of labor laws;

h) follow up and support labor relation of enterprises situated in more than one Region;

i) establish a system to prevent occupational accidents and occupational diseases; issue occupational health and safety standards and supervise their implementation;

j) establish a system to ensure industrial peace and ensure its proper implementation;

https://chilot.me



ተ) አሠሪዎችና ሠራተኞች በማህበር የመደራጀትና የኅብረት ድርድር የማድረግ መብቶቻቸውን እንዲጠቀሙ ያበረታታል፣ ይደግፋል፣ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚደራጁትን የሠራተኛና የአሠሪ ማህበራት ይመዘግባል፤

ቸ) በአሠሪዎችና በሠራተኞች መካከል የሁለትዮሽ፣ እንዲሁም የመንግሥት ወገንን ጨምሮ የሶስትዮሽ የውይይት መድረኮች እንዲደረጉ ድጋፍ ያደርጋል፤ የሥራ ክርክሮችን ክስተት ለመቀነስ የሚያስችሉ ስልቶችን ይቀይሳል፤ ሲከሰቱም መፍትሄ የሚያገኙበትን የተቀላጠፈ የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ያስፈጽማል፤

ኀ) በአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተሞች ውስጥ የሚገኙ የፌደራል መንግሥት የልማት ድርጅቶችን የሚመለከቱ የሠራተኛ ማህበራትንና የኅብረት ስምምነቶችን ይመዘግባል፤ በእነዚሁ ድርጅቶች ውስጥ የሥራ ሁኔታ ቁጥጥር አገልግሎት ተግባሮችን ያከናውናል፤ በአሠሪዎችና በሠራተኞች መካከል የሚነሱ የሥራ ክርክሮችን በስምምነት ለመጨረስ የማስማማት አገልግሎት ይሰጣል፤

ነ) የአሠሪና ሠራተኛ ብሔራዊ የመረጃ ሥርዓት ይዘረጋል፣ ሀገራዊ የሥራ ገበያ መረጃ ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣ የሥራ ፈላጊዎችን መረጃ ይይዛል፣ ሀገራዊ የሥራ እድል ፈጠራ ሥራዎች እንዲበረታቱ የሚያደርግ የእውቅናና የማበረታቻ ሥርዓት ይዘረጋል፣ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

k) encourage and support employers and workers to form associations and thereby exercise their rights of collective bargaining; register employers' association and trade unions established at national level;

l) support the practice of bipartite forums between employees and employers and tripartite forums involving the Government; devise mechanism to minimize occurrence of labor disputes and establish efficient system for settlement of the same;

m) register trade unions and collective agreements relating to Federal Public Enterprises situated in Addis Ababa and Dire Dawa cities; carry out labor inspection services in such enterprises; provide conciliation services to amicably settle labor disputes arising between employers and workers;

n) establish national labor sector information system; establish and put into operation a national labor market information system; keep job seekers data; establish system of recognition appreciation to encourage national job creation; follows up the implementation of the same;

https://chilot.me



ኘ) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር መደበኛ ያልሆነውን የኢኮኖሚ ዘርፍ ወደ መደበኛ ኢኮኖሚ ለማሸጋገር የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

አ) ለውጭ ሀገር ዜጎች የሥራ ፈቃድ ይሰጣል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር አፈጻጸሙን ይቆጣጠራል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የኢትዮጵያዊያንን የውጭ ሀገር የሥራ ስምሪት ይቆጣጠራል፤

ከ) የሥራ እድል ፈጠራን በተመለከተ የገጠር የሥራ እድል ፈጠራን ጨምሮ በተለያዩ ዘርፎች የሚሰሩ ሥራዎችን በበላይነት ያስተባብራል፣ ይከታተላል፤ ሪፖርት እንዲቀርብለት ያደርጋል፤

ኸ) ከክልሎች የሚመለከታቸው ኤጀንሲዎች ጋር በመተባበር በሥራ ገበያ ላይ የሚታዩ የክህሎት ክፍተቶችን በተመለከተ ወቅታዊ የዳሰሳ ጥናቶችን ያካሂዳል፤ የአቅም ግንባታ ሥልጠናዎችን ያስተባብራል፤

ወ) የሥራ እድልን ለማስፋፋት በፌደራል እና ክልል መንግሥት አካላት፣ የግል ዘርፍ፣ መደበኛ ባልሆነው ዘርፍ፣ የልማት አጋሮች እና ተቋማት መካከል ትብብር እንዲኖር ያግዛል፣ ያስተባብራል፣ ሥልጠናዎች እና የሥራ ልምዶች ከሥራ ገበያ ፍላጎቶች ጋር የተጣጣሙ እንዲሆኑ ይሰራል፤

o) devise, in collaboration with concerned organs, system that will enable the transition of the informal economic sector to the formal one; follow up implementation of the same;

p) issue work permits to foreign nationals and, monitor the compliance therewith in collaboration with concerned organs; regulate the Ethiopians overseas employment in collaboration with concerned organs;

q) coordinate and follow up the job creation initiatives including rural job creation conducted by different sectors, shall force others to send report;

r) conduct periodic surveys on labor market skills gap in collaboration with regional concerned agencies, coordinate capacity building trainings,

s) support and coordinate cooperation between agencies of the Federal government, regional governments, the private sector, the informal sector, development partners and institutions to promote and increase access to employment; ensure training and work experiences match the job market requirements;

https://chilot.me



ዐ) ከሚመለከተው አካል ጋር በመተባበር ለሥራ ፈጣሪዎች እና ፈላጊዎች አስፈላጊውን የንግድ ሥራ ልማት አገልግሎትና ኢንተርፕሬነርሺፕ ሥልጠናና ድጋፍ እንዲሰጥ ያደርጋል፣ ለጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች አማራጭ የፋይናንስ ምንጭ የሚያገኙበት ሥርዓት ይዘረጋል፣

ዘ) ለሥራ ፈላጊዎች ቅጥር እና ምደባ በመደበኛ እና መደበኛ ባልሆነ የቅጥር ዓይነት በሀገር ውስጥ እና በውጭ ሀገር እንዲመቻቹ ያደርጋል፤

ዠ) አካል ጉዳተኞች የተለየ የክህሎት ሥልጠና እንዲያገኙ ያመቻቻል፤

የ) ከድህነት ወለል በታች ላሉ ዜጎች ልዩ ፓኬጅ ተቀርጾ ወደ ሥራ እንዲሰማሩ በማድረግ በጊዜ ገደብ ወደ ተሻለ ደረጃ እንዲሸጋገሩ ያስተባብራል፤

ደ) ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር የግልና የመንግሥት ተቋማት የሚገኙ ድጋፎችን ያስተባብራል፡፡

፪/ በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች፡-

ሀ) ለሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የተሰጡ አሠሪና ሠራተኛን የሚመለከቱ ሥልጣንና ተግባራት፣

ለ) ለሥራ እድል ፈጠራ ኮሚሽን ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባራት፣

t) ensure, in collaboration with concerned organs, the provision of business development services and entrepreneurship training and support to promote job creations and employment opportunities; establish a system of alternative financial sources for micro, small and medium entrepreneurships;

u) cause the facilitation of employment and placement of job seekers in formal and informal employment domestically and overseas;

v) create conducive condition for skill development for disabled persons;

w) formulate a special package for the citizen who are under poverty line and assist them to be engaged in different jobs and graduate in specific time frame;

x) coordinate supports to be obtained from domestic and foreign, private and government institutions having similar objectives.

2/ The powers and duties entrusted to:

a) the Ministry of labor and social affairs with regard to labor relation

b) the job creation commission

https://chilot.me


ሐ) ለፌደራል ከተሞች የሥራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ሥራ ፈጠራን የሚመለከቱ ሥልጣንና ተግባራት፣

በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

c) the Federal Urban Job Creation and Food Security Agency with regard to job creation,

under other laws that are currently in force are hereby vested in the Ministry of Labor and Skills established under this Proclamation.

## ፳፮. የገንዘብ ሚኒስቴር

፩/ የገንዘብ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

ሀ) ለፊስካል በተለይም ለታክስና ለቀረጥ ሕጎች መሠረት የሚሆኑ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችና ሕጎችን ያመነጫል፣ ለአፈጻጸሙ ዝርዝር ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ መርሀ-ግብር ያዘጋጃል፣ በትክክል በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤

ለ) የፌደራል መንግስትን በጀት ያዘጋጃል፣ በተፈቀደው በጀት መሠረት ክፍያ ይፈጽማል፣ የበጀቱን አፈጻጸም ይገመግማል፤

ሐ) ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የፌደራል መንግሥትን የበጀት፣ የሂሣብ አያያዝ፣ የክፍያና የውስጥ ኦዲት ሥርዓት ይዘረጋል፣ የአፈጻጸሙን ውጤታማነት ይከታተላል፤ የፌደራል መንግስት እና የክልል መስተዳድር የበጀት፣ የሂሣብ አያያዝ፣ የክፍያና የውስጥ ኦዲት ሥርዓቶች አንድ ወጥና የተጣጣሙ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

## 26. Ministry of Finance

1/ The Ministry of Finance shall have the following powers and duties:

a) initiate policies, strategies and laws that serve as a base for fiscal, particularly for taxes and custom duty laws; prepare detail program compatible with national development plan; follow up the proper implementation of the same;

b) prepare the fiscal budget of the Federal Government; make disbursements in accordance with the approved budget; evaluate the utilization of the budget;

c) establish budgeting, accounting, disbursement and internal audit systems aligned with international standards for the Federal Government, and follow up the effectiveness of the implementation of the same; ensure that budgeting, accounting, disbursement and internal audit system of the federal and regional government is harmonized.

https://chilot.me



መ) የፌደራል መንግሥቱን የግዢና የንብረት አስተዳደር ሥርዓት መዘርጋቱንና በሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፤

ሠ) የፌደራል መንግሥት አክሲዮኖችን፣ የሚተላለፉና የማይተላለፉ የገንዘብ ሰነዶችንና ሌሎች ተመሳሳይ ተቀማጭ የገንዘብ ሀብቶችን ይይዛል፣ ይጠብቃል፤ ፈንዶችን ያስተዳድራል፣ በሌሎች ዘርፎች የሚተዳደሩ ፈንዶች ለታለመላቸው ዓላማ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

ረ) ከተለያዩ መንግሥታት ጋር የሚደረገውን የሁለትዮሽ ኢኮኖሚ ትብብር እንዲሁም የኢኮኖሚ ትስስር ለመፍጠር ከተቋቋሙ ዓለም አቀፍና አህጉራዊ ድርጅቶች ጋር የሚደረገውን ግንኙነት ይመራል፣ ያስተባብራል፤ የዚህ ዓይነቱ ትስስር በሀገሪቱ የኢኮኖሚ አፈጻጸም ላይ የሚኖረውን ውጤት ይከታተላል፤

ሰ) የውጭ እርዳታና ብድር ያሰባስባል፣ ይደራደራል፣ ይፈርማል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

ሸ) የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ፕራይቬታይዝ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ሰነዶችን ያዘጋጃል፤ ከሚመለከታቸው የመንግሥት ተቋማት ጋር በመቀናጀት የፕራይቬታይዜሽን ሂደቱን ያስተባብራል።

፪/ በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች ለገንዘብ ሚኒስቴር የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው ገንዘብ ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

d) ensure the establishment of a procurement and property management system of the Federal Government and follow up its implementation;

e) be the depository of and safeguard the Federal Government's shares, negotiable and non-negotiable instruments and other similar financial assets; administer funds, ascertain the fulfillment of the objectives of funds administered by other sectors.

f) Lead and coordinate bilateral economic cooperation with other countries as well as the relationship with international and regional organizations setup to create economic cooperation; follow up the impact of such links on the performance of the country's economy;

g) mobilize, negotiate and sign foreign assistance and loans, and follow up the implementation of the same:

h) prepare documents necessary to privatize public enterprises; coordinate privatization processes in collaboration with concerned government bodies;

2/ The powers and duties entrusted to the Ministry of Finance under other laws that are currently in force are hereby vested in the Ministry of Finance established by this Proclamation.

https://chilot.me



## ፳፯. <u>የገቢዎች ሚኒስቴር</u>

፩/ የገቢዎች ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

ሀ) የፌደራል ሀገር ውስጥ ገቢ አፈጻጸም ለማሻሻል እና ገቢ በአግባቡ እንዲሰበሰብ ለማድረግ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን ያካሂዳል፤ በጥናትና ምርምር ውጤት መሠረት ስትራቴጅዎችን ይቀርጻል፣ የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፤

ለ) የፌደራል ሀገር ውስጥ ገቢ የመሰብሰብ አቅም ግንባታን በቀጣይነት የሚያረጋግጡ አሠራሮችን ይቀርጻል፤ ይተገብራል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

ሐ) ዘመናዊ የሀገር ውስጥ ገቢ አወሳሰንና አሰባሰብ ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ያደርጋል፤

መ) ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት ለባለሀብቶች የተሰጡ የታክስ እፎይታ መብቶች በአግባቡ እንዲፈጸሙ ያደርጋል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤ በአግባቡ በማይጠቀሙት ላይ እርምጃ ይወስዳል፤

ሠ) ታክስ ከፋዮች በፍቃደኝነት ታክስ የመክፈል ባህልን እንዲያዳብሩ የሚያግዝ ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ያደርጋል፤

ረ) ለታክስ አወሳሰን የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ይሰበስባል፤ ይተነትናል፣ ጥቅም ላይ ያውላል፣

## 27. <u>Ministry of Revenue</u>

1/ The Ministry of Revenue shall have the following powers and duties:

a) conduct study and research activities to improve the performance of federal government revenues and proper collection of revenues; based on the result of the study devise a strategy and establish a system for its implementation;

b) formulate a system for building the capacity of collection of federal revenue in a sustainable manner; implement the same and follow up its implementation;

c) establish a modern revenue assessment and collection system and implement the same;

d) cause the proper implementation of incentives of customs and tax exemptions given to investors to encourage investment and follow up its implementation and take measures on those who misuse the exemption;

e) implement awareness creation programs to promote a culture of voluntary compliance of taxpayers in the discharge of their tax obligations by establishing a system;

f) collect information for tax assessment and analyze and use such information for the same;

https://chilot.me



ሰ) የታክስ ሕጎችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ በማናቸውም ግለሰብ ወይም ድርጅት እጅ የሚገኙ ሰነዶችን ይመረምራል፤ ይይዛል፣

ሸ) ለክልል የገቢ ሰብሳቢ አካላት ተገቢውን የአቅም ግንባታ ድጋፍ በመስጠት የፌደራልና የክልል ታክስ አስተዳደር ሥርዓት የሚጣጣሙበትን ሁኔታ ይፈጥራል፤

ቀ) ለሎተሪ ሥራ ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፣ ይሰርዛል፤

በ) የሎተሪን ጨዋታ ለማካሄድ የሚያስፈልጉ የመሳሪያ ዓይነቶችና መመዘኛዎችን ይወስናል፣ ወደ ሀገር የማስገቢያ ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፤

ተ) ሕገ-ወጥ የሎተሪ ሥራዎችን ይቆጣጠራል፤

ቸ) ለክልል ገቢ ሰብሳቢ አካላት ተገቢውን የአቅም ግንባታ ድጋፍ በመስጠት የፌደራል እና ለፌደራል መንግስት ተጠሪ ለሆኑ የከተማ አስተዳደሮች እና የክልል መንግስታት የታክስ አስተዳደር ሥርዓቶች የሚጣጣሙበትን ሁኔታ ይፈጥራል፤

ኀ) በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች የፌደራል ሀገር ውስጥ ገቢን እና ታክስን በተመለከተ ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉሙሩክ ባለሥልጣን የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

፪/ በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች የፌደራል ሀገር ውስጥ ገቢን እና ታክስን በተመለከተ ለገቢዎች ሚኒስቴር የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው ገቢዎች ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

g) inspect and seize documents under the possession of any person that are required for the enforcement of tax laws;

h) provide appropriate capacity building support to regional revenue collecting agencies with a view to harmonizing federal and regional tax administration systems;

i) issue permit to undertake lottery activity, supervise, suspend and revoke the same;

j) determine the type and specifications of equipment required to perform lottery games; issue permit and supervise the importation of the same;

k) control illegal lottery activities;

l) provide appropriate capacity building support to regional revenue collecting agencies with a view to harmonizing federal. city administration a accountable to the federal government and regional tax administration systems;

m) implement the powers and duties entrusted to Ethiopian revenue and customs authority under other laws that are currently in force with respect to federal revenue and taxes;

2/ The powers and duties entrusted to the Ministry of Revenue under other laws that are currently in force with respect to revenue and tax are hereby vested in the Ministry of Revenue established by this Proclamation;

https://chilot.me


## ፳፰. የፕላንና ልማት ሚኒስቴር

፩/ የፕላንና ልማት ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ) የልማት፣ የሀገራዊ የስታቲስቲክስ፣ የሥነ-ሕዝብ፣ የአየር ንብረት ለውጥንና አካባቢን የሚመለከቱ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ሕጎችን ያመነጫል፣ ለአፈጻጸሙ ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርሀ-ግብር ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

ለ) ሀገራዊ የረጅም ዘመን አመላካች የልማት ፕላን ያዘጋጃል፣ በዚህም ላይ ተመስርቶ የሀገሪቱን የአጭርና የመካከለኛ ዘመን የልማት ፕላንና ፕሮግራም ያዘጋጃል፣ ሥራ ላይ እንዲውል ይመራል፤

ሐ) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የልማት ፕላን አካል የሆነውን ሀገራዊ የኢኮኖሚ እድገት ትንበያና የማክሮ ኢኮኖሚ ማዕቀፍ ያዘጋጃል፤ ከማክሮ ኢኮኖሚ ማዕቀፉ የተጣጣሙ የቁጠባ፣ የኢንቨስትመንት እና የወጪና የገቢ ንግድ የማክሮ ኢኮኖሚ ግቦችን ያዘጋጃል፤

መ) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በመላ ሀገሪቱ የተመጣጠነ ልማት እና ውጤታማ የመሬት አጠቃቀምን ለማሳካት ሀገራዊ የስፓሻል ፕላን ያዘጋጃል፤ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

## 28. Ministry of Planning and Development

1/ The Ministry of Planning and Development shall have the following power and duties:

a) initiate policies, strategies and laws with respect to development, national statistics, population, climate change and environment; prepare detail program compatible with national development plan and implement the same upon approval;

b) prepare long-term indicative development plan, formulate medium and short-term development programs on the basis of the plan and oversee its implementation;

c) prepare, in collaboration with concerned organs, frameworks for macro-economy and the forecasting of economic growth; formulate saving, investment, import and export economic goals in line with the macro-economic framework;

d) prepare, in collaboration with the concerned organs, spatial development framework which ensures equitable development and effective land use; follow up its implementation;

https://chilot.me



ሠ) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የክልሎችንና የዜጎችን ፍትሐዊ የመልማትና የልማት ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያግዝ ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

ረ) የኢኮኖሚና የልማት ፖሊሲ ትንተናና ጥናቶች ያካሂዳል፣ ስትራቴጂካዊ የሶሺዮ-ኢኮኖሚ ጉዳዮችን ይለያል፤ በትንተናና ጥናቶች በሚገኙ ውጤቶች መሠረት የፖሊሲ ምክረ ሀሳቦችን ለሚመለከተው የመንግሥት አካል ያቀርባል፤በተለያዩ አካላት የሚመነጩ የልማት ፖሊሲዎችን የተጣጣሙ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

ሰ) የፖሊሲ ጥናትና ምርምር ሥራዎችን ያስተባብራል፤

ሸ) የልማት ፕላንን ለማሳካት እንዲሁም የመንግስት የማስፈጸም አቅም ለማጠናከርና ቀጣይነት ያለው ተቋማዊ አቅም እንዲፈጠር የአስፈጻሚ ተቋማት ሪፎርም እና የሥርዓት ማሻሻያ ጥናት ያካሂዳል፣ በጥናቱ ላይ ተመስርቶ የፌደራል መንግስት ተቋማትን ዓላማ፣ ተልዕኮ፣ ሥልጣንና ኃላፊነትን፣ በተመለከተ የውሳኔ ሀሳብ ለመንግስት ያቀርባል፤

ቀ) በመንግሥት በጀት፣ በመንግስት ዋስትና ብድር እንዲሁም በሌሎች ተመሳሳይ የበጀት ምንጮች እንዲከናወኑ የታቀዱ የፌደራል መንግስት የልማት ፕሮጀክቶች ላይ የአዋጭነትና አስፈላጊነት ግምገማ ያካሂዳል፣ የልማት ፕሮጀክቶችን ቅደም ተከተል ያስይዛል፣ የልማት ፕሮጀክቶችን የሱፐርቪዥን ሥራ ይመራል፣ አፈጻጸማቸውንም ይከታተላል፣ ይገመግማል፤

e) establish, in collaboration with concerned organs, a system which ensure equitable development opportunities and equitable development of regions and citizens; follow up its implementation;

f) conduct economic and development polices analysis and researches; identify strategic socio-economic issues; based on findings from socio-economic researches propose policy to relevant government organs; ensure the compatibility of policies initiated by different organs;

g) coordinate policies' research and development initiatives;

h) conduct researches related to executive organs and system reform in order to achieve development plans, strengthen government enforcement capacity and create sustainable institutional capacity; proposes recommendations, based on researches, to the government regarding the scope of powers and duties and organizational structures of federal government institutions;

i) conducts development project appraisal on development projects which are financed from treasury, sovereign guarantee, loan and other similar budgetary sources; select and prioritize development projects; lead the supervision of development projects, monitor and evaluate development project implementation;

https://chilot.me


በ) የሀገሪቱን የልማት ፕላን ለማስፈጸም የሚያግዙ የልማት ፕሮጀክቶችን በመለየትና በመቅረጽ በሚመለከታቸው አስፈጻሚ አካላት ተጨማሪ ዝግጅቶች ተደርጎባቸው ተግባራዊ እንዲደረጉ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤

ተ) የልማት ፕላን፣ ፕሮግራም እና ፕሮጀክቶች አዘገጃጀት ሥርዓት ይዘረጋል፣ ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣ የቴክኒካል ምክር አገልግሎትና የአቅም ግንባታ ድጋፍ ይሰጣል፤

ቸ) ሀገራዊ የልማት ፕላን፣ ፕሮግራም እና ፕሮጀክቶች አፈጻጸም በየጊዜው ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ የሀገራዊ የልማት ሥራዎች አፈጻጸም ሪፖርት በማዘጋጀት ለመንግሥት ያቀርባል፤

ኀ) የልማት ፕላን፣ ፕሮግራም እና ፕሮጀክቶች የአፈጻጸም ክትትል እና ግምገማ ሥርዓት እና አጋዥ መሠረተ ልማት ይዘረጋል፣ ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣ የቴክኒካል ምክር አገልግሎትና የአቅም ግንባታ ድጋፍ ይሰጣል፤

ነ) የብሔራዊ የኢኮኖሚ አካውንትና ስታቲስቲክስ በማዘጋጀት ዓመታዊና የሩብ ዓመት ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ግመታ ያካሂዳል፣ የተጣጣመ እና ደረጃውን የጠበቀ ክልላዊ የኢኮኖሚ አካውንት ሥርዓት ይዘረጋል፣ ክልሎች የራሳቸውን የኢኮኖሚ አካውንት እንዲያዘጋጁ የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፤

j) identify and formulate development projects for the implementation of national development plan and support and monitor their implementation by the relevant executive organs;

k) establish system for the formulation of development plans, programs and projects; cause the implementation of the same; provide technical support and capacity building on the system;

l) follow up and evaluate national development plan program and project performance; submit national development activities implementation report to the government;

m) establish performance follow up and evaluation system and supporting infrastructure; implement the same; provide technical advice service and capacity building support;

n) establish system for the accounting of national economic account statistics and estimate quarterly and annual gross domestic product; establish harmonized and standardized regional economic accounting system; provide technical support to regions to enable them prepare their own regional economic accounts;

https://chilot.me



ኘ) የዓለም አቀፍ ስታቲስቲክስ ስታንዳርዶችን መሠረት በማድረግ ሀገራዊ የስታቲስቲክስ ሥርዓት፣ ስታንዳርድ እና ደንብ ያዘጋጃል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

አ) በኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት የሚሰበሰቡትን ሀገራዊ የስታቲስቲክስ መረጃዎችን በተመለከተ ትርጉምና ደረጃ ያወጣል፣ የሚሰበሰበውን መረጃ ዓይነት እና የስታቲስቲክስ ካሌንደር ይወስናል፣ በዚሁ መሠረት መከናወናቸውን ይከታተላል፤

ከ) ኦፊሴላዊ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ እና ሥነ-ሕዝብ ስታቲስቲክስ የመረጃ ጥራት ክትትል ያደርጋል፤ ይገመግማል፣ እውቅና ይሰጣል፤

ኸ) ዓለም አቀፍ ስታቲስቲካዊ ደረጃን ለመጠበቅ በሀገሪቱ የሚሰበሰቡ ስታቲስቲካዊ መረጃዎች ከሌሎች ሀገሮች፤ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች እና ከተባበሩት መንግስታት ድርጅት ጋር ተነጻጻሪ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

ወ) የሌሎች ተቋማት መረጃ የመሰብሰብ ተግባራት ይቆጣጠራል፣ የአሠራር ስታንዳርድ እና የናሙና ዘዴያቸውን ያጸድቃል፤ የትክክለኛነት ማረጋገጫ ይሰጣል፤

ዐ) የአካባቢና የአየር ንብረት ለውጥን የሚመለከቱ ሥራዎችን ይደግፋል፣ ይካታተላል፣ ያስተባብራል፤

o) establishes national statistical systems, standards and regulations in accordance with international statistical standards and follow up its implementation;

p) issue, interpretation and standards regarding national statistical data collected by Ethiopian Statistical Service; determine the type of data to be collected and determine the statistical calendar; follow up its implementation;

q) follow up, evaluate and authorize the quality of official economic, social and population national statistical data;

r) in order to maintain international statistical standards, cause statistical data collected in the country to be comparable to those of other countries, international organizations and United Nations Institutions with statistical data;

s) regulate data collection of other institutions and approve survey systems and methodologies; provide authentication on the same;

t) coordinate, support and follow up climate change and environment activities.

https://chilot.me


፪/ በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች ለፕላንና ልማት ኮሚሽን የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው ፕላንና ልማት ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

**፳፱. <u>የኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር</u>**

፩/ የኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

ሀ) የባዮና ኢመርጂንግ ቴክኖሎጂ፣ የጂኦ ስፓሻል፣ የስፔስ፣ የቴክኖሎጂ እና ዲጂታል ኢኮኖሚ ልማትንና ተወዳዳሪነትን በቀጣይነት የሚያረጋግጡ፣ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎች፣ ሕጎችንና ፕሮግራሞች ይቀርጻል፣ ለአፈጻጸሙ ዝርዝር ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ መርሀ-ግብር ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

ለ) ከሚመለካታቸው አካላት ጋር በመተባበር የሳይንስ፣ የቴክኖሎጂ እና የኢኖቬሽን አጠቃቀም ባህል እንዲጎለብት የሚያስችል ፖሊሲ ያመነጫል፣ በሚመለከተው አካል ሲጸደቅም ተግባራዊ መደረጉን ይከታተላል፤የሀገሪቱ ሥርዓተ- ትምህርት እና ሥርዓተ- ሥልጠና ከኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት አንጻር መቃኘቱን ያረጋግጣል፤

2/ The powers and duties entrusted to the Planning and Development Commission under other laws that are currently in force are hereby vested in the Ministry of Planning and Development established by this Proclamation.

**29. <u>Ministry of Innovation and Technology</u>**

1/ The Ministry of Innovation and Technology shall have the following powers and duties:

a) initiate policies, strategies, laws and programs that sustainably ensure the development and competitiveness bio and emerging technology, geospatial, space, technology and digital economic development; prepare a detail program that is compatible with the country's overall development plan and implement the same upon approval;

b) initiate policy, in collaboration with the concerned organs, for the enhancement of technology and innovation use culture; ensure, in collaboration with the concerned organs, the country's educational curricula are designed in tune with innovation and technology development;

https://chilot.me


ሐ) የሀገራዊ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ምርምርና ልማት ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን እና ፕሮግራሞችን ያዘጋጃል፣ ያስፈጽማል፣ ለሀገሪቱ እድገት አስፈላጊ የሆኑ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ የጥናትና ምርምር መስኮችን ይለያል፤ ሀገራዊ የምርምር ፕሮግራሞችን ያስተባብራል፤

መ) በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ዘርፍ ልማት የግል ዘርፉን ተሳትፎና ሚና ለማሳደግ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ለአፈጻጸሙ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፣ ለኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማትና ለፈጠራ ሥራዎች እድገት አስተዋጽኦ ላበረከቱ ግለሰቦችና ተቋማት ሽልማትና ማበረታቻ የሚሰጥበትን ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊም ያደርጋል፤

ሠ) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አገልግሎቶች ጥራታቸው፣ ደህንነታቸውና አስተማማኝ ነታቸው የተጠበቀ እንዲሆን የሚያስችሉ ደረጃዎችን ይወስናል፣ ተግባራዊ መደረጋቸውንም ይቆጣጠራል፤

ረ) በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ ተቋማትና ባለሙያዎች አቅም ግንባታን ይደግፋል፤ የሙያ ማህበራትንና የጥናትና ምርምር ተቋማትን ይደግፋል፣ ያበረታታል፤

c) prepare and implement national innovation and technology research and development policies, strategies and programs; identify new innovation and technology studies and research areas pertinent to the national development; coordinate national research programs;

d) establish a system that enhance the participation and role of the private sector in the development of innovation and technology sector; create conducive condition for implementation of the same; establish and implement a system for the grant of awards and incentives to individuals and institutions contributing to the advancement of innovation and technological development works;

e) set, in collaboration with concerned organs, standards to ensure the provision of quality, reliablity and security of information communication technology services; monitor the implementation of the same;

f) support capacity building of institutions and professionals involved in innovation and technology activities; support and encourage professional associations and research and study institutions;

https://chilot.me



ሰ) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የቴክኖሎጂ ፍላጎት ለመዳሰስ፣ ተገቢ ቴክኖሎጂዎችን ለማፈላለግና በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

ሸ) ሀገር-በቀል ቴክኖሎጂዎችን ለማሻሻል፣ ለማሳደግና ለገበያ ለማቅረብ የሚደረጉ ጥናቶችን፣ የምርምርና ስርጸት ሥራዎችን ያበረታታል፣ ወደተግባር እንዲሸጋገሩ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፤ በፕሮቶታይፕ፣ ለባለድርሻ አካላትና ለማህበረሰቡ ተደራሽ ያደርጋል፤ ለኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ መዳበር የበለጠ አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ ግለሰቦችን፣ የሙያ ማህበራትንና የጥናትና ምርምር ተቋማትን ያበረታታል፣ ይደግፋል፤

ቀ) በየዘርፉ በሽግግር የሚመጡ ቴክኖሎጂዎችን መረጃ ይመዘግባል፣ የማጠቃለልና የማቀብ ሥራዎችን ያስተባብራል፣ ለቀጣይ ሥራ እንዲውሉ ያደርጋል፤

g) establish, in collaboration with the concerned organs, a system to identify technology demand, explore appropriate technologies and implement the same; follow up the implementation of the same;

h) support studies, researches and their dissemination, for the improvement, development and marketing of indigenous technologies; provide necessary support for practical application of such works; cause them accessible to stakeholders and the community in the form of prototype; encourage and support individuals, professional associations, study and research institutions that will make significant contribution for the development of innovations and technologies;

i) register information about technologies from different fields; coordinate works for their compilation and preservation; cause them to be used for future works;

https://chilot.me


በ) የኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ በተለይ የዲጂታል መሠረተ ልማቶች ለማስፋፋት የሚያስችሉ ፕሮግራሞችን በመቅረጽ ተግባራዊ ያደርጋል፤ ለሕዝብ አገልግሎት በመስጠት ላይ ያተኮሩ መሠረታዊ የአሠራር ሥርዓትና አገልግሎቶች በቴክኖሎጂ የሚደገፉበትንና ለተጠቃሚዎች የተሻለ አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉበትን ሁኔታ መመቻቸታቸውን ያረጋግጣል፤ በአጠቃላይ የመንግስት አገልግሎት በቴክኖሎጂ የተደገፈና ቀልጣፋ እንዲሆን ይሰራል፣ ድጋፍ ያደርጋል፤

ተ) የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ መረጃ ቋት ያደራጃል፣ መረጃዎችን ያጠናቅራል፤ ሀገራዊ የመረጃ አያያዝ ደረጃ ያወጣል፤

ቸ) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የፌደራልና የክልል መስተዳደር ተቋማት የመረጃ ሥርዓትን ይገነባል፣ ያቀናጃል፤ ደህንነቱ የተጠበቀ የኢንፎርሜሽን መረብ የመዘርጋት ሥራን ይደግፋል፤

ኀ) ለተመረጡ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ምርምር የሚውሉ ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ ቤተ-ሙከራና የሰርቶ ማሳያ ማዕከላትንና የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ፓርኮችን በማቋቋም የሀገር ውስጥ የፈጠራ ክህሎት እንዲያድግ ድጋፍ ያደርጋል፤ለዚህም የሚያግዝ ስታርት አፕ ፈንድ እንዲቋቋም ያመቻቻል፤

i) design programs that enable the expansion of innovation and technology in particular digital infrastructures; ensure for critical systems and services in public sector are supported by appropriate technology and positioned to better provide services to the public; in general, works and provide support public services be supported by technology and efficient;

j) organize innovation and technology data base, compile information, set national standards for information management;

k) in collaboration with relevant bodies, support the development, and coordination of information systems; provide support for the deployment secured information network within federal and regional government institutions;

l) provide support for the promotion of domestic innovation skills through establishing internationally standardized laboratories, workshops and information communication technology parks for selected innovation and technology research works; facilitate for the establishment of start-up fund for the the same;

https://chilot.me


ነ) የጨረራና ጨረር አመንጪ ቁሶች አጠቃቀምና አወጋገድ ቁጥጥር ሥርዓት ተግባራዊ መደረጉን ይከታተላል፤

ኘ) ለክልሎች ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ተቋማት አቅም ግንባታ አስፈላጊውን የሙያና ቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፤ በክልሎች መከናወን ያለባቸውን የኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ልማት ተግባራትን በመለየት የጋራ መግባባት ተደርሶባቸው በየደረጃው ተግባራዊ እንዲደረጉ ያደርጋል፤ ተግባራዊ መደረጋቸውን ይከታተላል፤

አ) ፈጠራንና ኢኖቬሽንን በማበረታታት የፈጠራ ሀሳቦችን ወደ እሴት በመለወጥ ለሀገራዊ ብልጽግና የሚያደርጉት አስተዋጽኦ ውጤታማ እንዲሆን ይከታተላል፤

፪/ በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች ለኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

## ፴. <u>የትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ሚኒስቴር</u>

፩/ የትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

ሀ) የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ዘርፍ ልማትንና ተወዳዳሪነትን በቀጣይነት የሚያረጋግጡ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣ ፕሮግራሞችን እና ሕጎችን ያመነጫል፤ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

m) follow up the implementation of the system regulating the utilization and disposal of radiation and radiation producing items;

n) provide professional and technical support to regional innovation and technology institutions; identify and cause common understanding on innovation and technology development activities to be undertaken by the regions: follow implementation of the same;

o) follow up the effectiveness of the transformation of innovative ideas in to values role for national prosperity by supporting creativity and innovation;

2/ The powers and duties entrusted to the Ministry of Innovation and Technology under other laws that are currently in force are hereby vested in the Ministry of Innovation and Technology established by this Proclamation.

## 30. <u>Ministry of Transport and Logistics</u>

1/ The Ministry of Transport and Logistics shall have the following power and duties:

a) initiate policies, strategies, programs and laws that ensure sustainable development and competitiveness of the transport and logistics sector; implement the same upon approval;

https://chilot.me


ለ) የሀገሪቱን የልማት ስትራቴጂዎች ተግባራዊ ለማድረግ፣ የልማት ማዕከላትንና የእድገት ኮሪደሮችን የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ፍላጐት ለማሟላት የየብስ፣ የአየርና የባህር ትራንስፖርት አገልግሎቶች የተቀናጁ፣ ቀልጣፋና ተደራሽ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

ሐ) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ሁለንተናዊ ሀገራዊ የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ውህደት መናበብ እንዲፈጠር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ለአፈጻጸሙ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፤

መ) ከከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር እና ሌሎች ሚመለካታቸው አካላት ጋር በመተባበር የሀገሪቱን የተቀናጀ የትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ መሠረተ ልማቶች ማስተር ፕላን ያዘጋጃል፣ ተግባራዊ መደረጋቸውን ይከታተላል፤

ሠ) በትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ዘርፍ ልማት የግል ዘርፉን ተሳትፎና ሚና ለማሳደግ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ለአፈጻጸሙ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፤

ረ) የትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት አሰጣጥ የደህንነት ደረጃዎችን ያዘጋጃል፤ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፤ ተግባራዊ እንዲደረጉ ያደርጋል፤

b) ensure the integration, efficiency and accessibility of land, air and sea transportation services, and thereby realize the country's development strategies and meet the needs of transport and logistics of development hubs and corridors;

c) establish, in collaboration with concerned organs, a system for a coordinated and integrated holistic national transport and logistics; create conducive conditions for implementation of the same;

d) in collaboration with Ministry of Urban and infrastructure and other concerned organs, prepare master plan of the country's transport and comprehensive logistics infrastructure; follow up its implementation;

e) establish a system that promote the participation and role of the private sector in transport and logistics development; create conducive condition for implementation of the same;

f) prepare safety standards for the provision of transport and logistics services; cause and follow up their implementation;

https://chilot.me


ሰ) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ዘርፍ ላይ በቀጣናዊ እና ዓለም አቀፍ ደረጃ ትብብር እንዲጎለብት ያደርጋል፣ በዘርፉ የትብብር ሥራዎችን ይመራል፤ የትብብር ስምምነት ለተደረሰባቸው ጉዳዮች ፕሮግራም ያዘጋጃል፣ ተግባራዊነቱን ያረጋግጣል፤

ሸ) ለሀገሪቱ ጠቀሜታ ያላቸውን አማራጭ የወደብ አገልግሎቶች እያጠና ለመንግስት ያቀርባል፣ ሲፈቀድም አፈጻጸሙን ይከታተላል፤ ከወደብ አገልግሎት ጋር በተያያዘ ከሌሎች ሀገራት ጋር የስምምነት ሰነዶችን ይፈራረማል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤

ቀ) የትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ መሠረተ ልማቶችን በተመለከተ አስተማማኝና ደህንነታቸው የተረጋገጠ እንዲሆኑ የሚያስችሉ የቁጥጥር ሥርዓቶችን እንዲዘረጉና ሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤

በ) በትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ዘርፉ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችና አሠራሮች በሀገር ውስጥ ጥቅም ላይ እንዲውሉ፣ እንዲስፋፉና እንዲዳብሩ ያደርጋል፤

g) cause, in collaboration with concerned organs, the promotion of regional and international cooperation in transport and logistics sector; lead cooperation function in the sector; prepare program for matters on which cooperative agreement is entered into; ensure the implementation of the same;

h) submit to the government studies on alternative port services and oversee their implementation when approved; conclude port service agreements with other countries and follow up its implementation:

i) ensure the establishment and implementation of regulatory frameworks to guarantee the provision of reliable and safe transport and logistics infrastructure;

j) cause the utilization, expansion and promotion of new technologies and practices in the country's transport and logistics sector;

https://chilot.me



ተ) የትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ መሠረተ ልማቶችና አገልግሎቶች በአካባቢና በአየር ንብረት የሚኖራቸውን ተጽዕኖ ለመቀነስ የሚያስችሉ ስልቶችን በመለየት ሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

k) identify and implement strategies to mitigate the impact of transport and logistics infrastructure and services on the environment and the climate;

ቸ) የሀገሪቱን የትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ መረጃዎች ያደራጃል፣ ለሚመለከታቸው አካላት ያሰራጫል፤

l) organize transport and logistics data of the country, and disseminate the same to concerned organs;

ኀ) የትራንስፖርት ማኔጅመንት ሥርዓቱን ለማሻሻልና የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ችግርን በመሠረታዊነት ለመፍታት የሚያስችሉ ጥናቶችን ያከናውናል ይተገብራል፤

m) undertake studies on transport management system aiming at improving and fundamentally addressing road traffic safety issues; implement the same;

ነ) የአውሮፕላን ትራንስፖርት አደጋ ምርመራ ተቀባይነት ባለው ደረጃ መሠረት መከናወኑን ያረጋግጣል፤

n) ensure that investigation of aircraft accidents are carried out in accordance with acceptable standards;

ኘ) የወጪና ገቢ ንግድ ሥራዎችን በተመለከተ የሀገሪቷን የሎጂስቲክስ ሥርዓት ቀልጣፋና ተወዳዳሪ መሆኑን ያረጋግጣል፤

o) ensure that the national logistic system with respect to import and export is efficient and competitive;

አ) በአዋጅ ቁጥር ፬፻፷፰/፲፱፻፺፯ ለፌደራል ትራንስፖርት ባለስልጣን የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት እንዲሁም በአዋጁ የተመለከቱትን አግባብነት ያላቸውን ሌሎች ድንጋጌዎች በሥራ ላይ ያውላል፤

p) implement the powers and duties entrusted to the Federal Transport Authority under Proclamation No. 468/2005 as well as other relevant provisions of the Proclamation;

https://chilot.me



ከ) በኢትዮጵያና በጅቡቲ መንግስታት መካከል በተፈረሙ የሁለትዮሽ ስምምነቶች መሠረት የተቋቋሙት የምድር ባቡር ድርጅቶችን የሥራ እንቅስቃሴዎች በሁለቱ ሀገሮች መካከል በተደረጉት ስምምነቶች መሠረት ይከታተላል፡፡ በበላይነት ይቆጣጠራል፡፡

፪/ በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች ለፌደራል ትራንስፖርት ባለስልጣንና ለትራንስፖርት ሚኒስቴር የተሰጡ ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስን የተመለከቱ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

**፴፩. <u>የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር</u>**

፩/ የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ) የከተማና ኮንስትራክሽንና መሠረተ ልማትን ተወዳዳሪነትን በቀጣይነት የሚያረጋግጡ እና መሠረተ ልማት በውጤታማነትና በቅንጅት መከናወኑን የሚያረጋግጡ፣ የከተማ መሬትን እና ከመሬት ጋር የተያያዘ ሌላ የማይንቀሳቀስ ንብረት ለመመዝገብ የሚያስችሉ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ሕጎችን ያመነጫል፣ ለአፈጻጸሙ ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርሀ-ግብር ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

q) follow up the operations of the Ethion-Djibouti Railways in accordance with the agreement concluded between the two countries; monitor the same.

2/ The powers and duties entrusted to the Ministry of Transport under other laws that are currently in force with respect to transport and logistics are hereby vested in the Ministry of Transport and Logistics established by this Proclamation;

**31. <u>The Ministry of Urban and Infrastructure</u>**

1/ The Ministry of Urban and Infrastructure shall have the following powers and duties:

a) initiate policies, strategies and laws that ensure sustainable competitiveness of urban and construction and infrastructure sustainable development; that ensure infrastructure development is carried out effectively and in an integrated manner; and that enable registration of urban land and land related other immovable property related to land; prepare detail program compatible with the national development plan for their implementation; implement the same upon approval;

https://chilot.me



ለ) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ሀገራዊ የተቀናጀ የመሠረተ ልማት፣ መዋቅራዊ እና ማስተር ፕላን ያዘጋጃል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

ሐ) ሀገራዊ የመንገድ መሠረተ ልማት ሥራዎች ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታነትንና ፍትሐዊ ተደራሽነትን መሠረት ባደረገ መልኩ መከናወናቸውን ይከታተላል፤

መ) በሀገር አቀፍ ደረጃ የከተሞች መዋቅራዊና መሠረታዊ ማስተር ፕላን ዝግጅትን ያስተባብራል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

ሠ) ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የሚለቀቅ የመሬት ይዞታ እና የንብረት ካሳ ቀመርና የነጠላ ዋጋ ያዘጋጃል፤

2/ The powers and duties entrusted to the Sport Commission and Ministry of Culture and Tourism with respect to culture and language under other laws that are currently in force are hereby vested in the Ministry of Culture and Sport established by this Proclamation.

**38. <u>Ministry of Defense</u>**

1/ The Ministry of Defense shall have the following powers and duties:

a) initiate policies, strategies and laws with respect to national defense building; implement the same upon approval;

b) defend, in collaboration with relevant organs, the territorial integrity of the country, protect and defend the Constitutional order form threats and attacks;

c) coordinate and work by coordinating relevant federal and regional organs in defending the country;

d) establish, equip and supervise defense forces, and ensure their combat capabilities;

e) cause the organization of defense forces training institutions;

https://chilot.me



ረ) የጦር ሠፈሮችንና ለሠራዊቱ የሚያስፈልጉትን የመኖሪያ ሠፈሮች ይሠራል፣ ያሠራል፤

ሰ) የሀገሪቱ የመከላከያ ሠራዊት የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የሕዝቦችን ሚዛናዊ ተዋጽኦ ያካተተ መሆኑን ያረጋግጣል፤

ሸ) የመከላከያ ሠራዊት ተግባር ለሕገ-መንግሥቱ ተገዢ እና ከፖለቲካ ድርጅት ወገናዊነት ነፃ በሆነ አኳኋን ማከናወኑን ያረጋግጣል፤

ቀ) ከክልል አቅም በላይ የሆነ የፀጥታ መደፍረስ ሲያጋጥም በክልሉ መስተዳድር ጥያቄ መሠረት ሠላምና መረጋጋትን ያሰፍናል፤

በ) ማንኛውም ክልል ሕገ-መንግሥቱን በመጣስ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን አደጋ ላይ ሲጥልና በሕገ-መንግሥቱ በተደነገገው መሠረት ሲታዘዝ ፀጥታንና ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን ያስከብራል፤

ተ) በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የሚሰጡትን ተግባሮች ያከናውናል፤

ቸ) የክተት አዋጅ በሚታወጅበት ጊዜ በሀገር ውስጥ የሚገኝ ሀብት በተቀናጀ ሁኔታ ጥቅም ላይ የሚውልበትን ዘዴ እያጠና ያስወስናል፤ ኅብረተሰቡ ከጠላት ጥቃት ራሱን የሚከላከልበትን ዕቅድ ያወጣል፣ ሲፈቀድም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

f) construct and cause the construction of military camps and residential quarters required for the defense forces;

g) ensure that the composition of the National Defense Forces reflect equitable representation of nations, nationalities and peoples;

h) ensure that it carries out its functions in accordance with the Constitution and free of any partisanship to any political organization;

i) secure peace and stability upon request by regional state administration where security situations that are beyond their control occur;

j) enforce, when commanded in accordance with the Constitution, security and constitutional order where any region violates the Constitution and endangers the constitutional order;

k) undertake the responsibilities assigned to it under State of Emergency Proclamations;

l) in the event of declaration of national mobilization, prepare plans and undertake study and cause the authorizations for the coordinated utilization of resources in the country; prepare plan whereby the public can defend or guard itself against enemy threats, and implement the same upon authorization, in collaboration with concerned organs;

https://chilot.me


ኀ) በጦርነት ወይም በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የመከላከያ ሠራዊትን የሚቀላቀል፣ እንዲሁም ሰው ሠራሽም ሆነ የተፈጥሮ አደጋዎች ሲከሰቱ እገዛ የሚያደርግ ብሔራዊ ተጠባባቂ ኃይል ይመለምላል፣ ያሰለጥናል፣ ያደራጃል፤

ነ) የሽምቅ ውጊያንና ሽብርተኝነትን ይከላከላል፤

ኘ) ሀገሪቱ የሚቀርብላትን ዓለም አቀፍ የሠላም ማስከበር ጥሪ በአግባቡ ለመወጣት የሚያስችል የሠላም አስከባሪ ኃይል ያደራጃል፣ ያሰማራል፤

አ) የሠራዊቱ አባላት በሠላም ጊዜ በሀገሪቱ የልማት ሥራዎች እንዲሳተፉ ያደርጋል፤

ከ) የመከላከያ ተቋማት በሠላም ጊዜ የሚኖራቸውን የማምረትና አገልግሎት የመስጠት ትርፍ አቅም በመጠቀም የሚያገኘውን ገቢ፣ ለመከላከያ ጠቀሜታ የማያስፈልጉ ንብረቶችን በማስወገድ የሚገኘውን ገቢ እና በተቆጣጣሪ ባለሥልጣንነት ከሚመራቸው ድርጅቶች የሚያገኘውን የትርፍ ድርሻ የሚኒስትሮች ምክር ቤትን እያስፈቀደ ለሀገር መከላከያ አቅም ግንባታ እንዲውል ያደርጋል፤

m) recruit, train and organize a national reserve force that joins the armed forces in time of war or state of emergency and that provides assistance in the event of man-made or natural disasters;

n) combat guerilla warfare and terrorism;

o) organize and deploy competent peace keeping forces that enable to participate in international peace keeping missions when a request is made to the country;

p) cause the participation of the defense forces in the country's development activities in times of peace;

q) upon obtaining the approval of the Council of Ministers, retain and utilize income derived from revenue generated by employing idle facilities of defense institutions in times of peace in income generating activities; the proceeds of disposal of properties which are no more required for defense purposes and dividends from enterprises put under its supervision for national defense capacity building;

https://chilot.me



ኸ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) ፊደል-ተራ (ከ) የተመለከተው ገንዘብ አስተዳደር በኢትዮጵያ ፌደራል መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፮፻፵፰/፪ሺ፩ እና በአዋጁ መሠረት በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የተደነገጉትን ሥርዓቶችና መመዘኛዎች ተከትሎ መፈጸሙን ያረጋግጣል፣ በዋናው ኦዲተርም እንዲመረመር ያደርጋል።

፪/ በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች ለመከላከያ ሚኒስቴር የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው መከላከያ ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

፴፱. **<u>የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር</u>**

፩/ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

ሀ) የኢትዮጵያን ሕዝቦች ጥቅም የሚያስጠብቅ፣ የሀገሪቱን ሉዓላዊነት የሚያስከብር፣ በጋራ ጥቅምና እኩልነት ላይ የተመሰረተ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን እና ሕጎችን ያመነጫል፣ ለአፈጻጸሙ ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርሀ-ግብር ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

ለ) ሀገሪቱ ባላት የውጭ ግንኙነት ጥቅሟና መብቷ እንዲጠበቅና በሌሎች መንግሥታት እንዲከበር ያደርጋል፤ ሀገሪቱ ከጎረቤት ሀገሮች ጋር ያላት መልካም ጉርብትና እንዲጠናከር ያደርጋል፤

r) ensure that the administration of the fund referred to in Sub-Article (1) paragraph (q) of this Article is carried out in accordance with the procedures and standards embodied in the Federal Government of Ethiopia Financial Administration Proclamation No. 648/2009 and, Regulations and Directives issued pursuant to the Proclamation, and submit same for auditing by the Auditor General.

2/ The powers and duties entrusted to the Ministry of Defense under other laws that are currently in force are hereby vested in the Ministry of Defense established by this Proclamation.

39. **<u>Ministry of Foreign Affairs</u>**

1/ The Ministry of Foreign Affairs shall have the following powers and duties:

a) initiate foreign policies, strategies and laws based on the principle of mutual respect and equality that protects the interests of the people of Ethiopia and safeguard its sovereignty; prepare a detail program compatible with the national development plan and implement the same upon approval;

b) safe guard the interests and rights of the country in connection with its foreign relations and ensure that they are respected by foreign states; ensure that the country's good relations with neighboring countries are strengthened;

https://chilot.me


ሐ) ሥልጣኑ በተለይ ለሌላ አካል በሕግ ካልተሰጠ በስተቀር፣ ኢትዮጵያ ከሌሎች መንግሥታትና ዓለም ዓቀፍ ድርጅቶች ጋር የምታደርጋቸውን በመንግሥት የተፈቀዱ ዓለም አቀፍ ውሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር ይደራደራል፣ ይፈርማል፤ እንዲሁም ዓለም አቀፍ ውሎች እንዲጸድቁ ለማድረግ የሚያስፈልጉትን ፎርማሊቲዎች ሁሉ ያከናውናል፤

መ) ሥልጣኑ በተለይ ለሌላ አካል ካልተሰጠ በስተቀር፣ የኢትዮጵያ መንግሥት የፈረማቸው ዓለም አቀፍ ውሎች የሚያስከትሏቸው መብቶችና ግዴታዎች መከበራቸውን ያረጋግጣል፤

ሠ) ሌሎች የመንግሥት አካላት ከውጭ ሀገር መንግሥታትና ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር የሚያደርጓቸውን ሁሉንም ግንኙነቶች ያስተባብራል፤

ረ) ኢትዮጵያ ከሌሎች መንግሥታትና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር የምታደርጋቸውን ዓለም አቀፍ ውሎች በሙሉ የተመሰከረላቸውን ዋናዎቹን ቅጂዎች መዝግቦ ይጠብቃል፤

ሰ) የኢትዮጵያ መንግሥት በብዙ መንግሥታት መካከል የሚደረጉ ዓለም አቀፍ ውሎችን አስቀማጭ በሚሆንበት ጊዜ ይኸው ባለአደራነት የሚጠይቀውን ተግባር ያከናውናል፤

c) without prejudice to power given by law to other organs, negotiate and sign, in consultation with relevant organs, treaties that Ethiopia enters into with other States and International organizations upon authorization by the Government; and effect all formalities required for ratification of international treaties;

d) ensure, without prejudice the powers entrusted to other organs, the enforcement of rights and obligations arising from treaties signed by the Government of Ethiopia;

e) coordinate all relations of other Government organs with Foreign States and international organizations;

f) register and keep all authentic copies of international treaties concluded between Ethiopia and other States and international organizations;

g) perform the functions of a depository of multilateral treaties when the Government of Ethiopia is a depository of such treaties;

https://chilot.me



ሸ) በኢትዮጵያ ከሚገኙ የውጭ ሀገራት መንግሥታት እንደራሴዎች፣ ቆንስሎችና የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ወኪሎች ጋር እንደአስፈላጊነቱ በመገናኘት የጋራ ጥቅሞች የሚጠበቁበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

ቀ) በዓለም አቀፍ ሕግና ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ ውሎች ለውጭ ሀገር መንግሥታት እንደራሴዎችና ለዓለም አቀፍ ድርጅቶች ወኪሎች የተሰጡ መብቶች እንዲከበሩ ያደርጋል፤

በ) በውጭ ሀገር የኢትዮጵያ የዲፕሎማቲክና የቆንስላ ሚስዮኖችን እንዲሁም በዓለም አቀፍ ድርጅቶች የኢትዮጵያ ቋሚ መልዕክተኞች ጽሕፈት ቤቶችን ተግባራት ያስተባብራል፣ ሥራቸውንም ይቆጣጠራል፤

ተ) አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የዲፕሎማቲክና ሰርቪስ ፓስፖርቶች እና የዲፕሎማቲክና ሰርቪስ መግቢያ ቪዛዎች ይሰጣል፤

ቸ) የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ በማካሄድ የሀገሪቱን የውጭ ንግድና ቱሪዝም ለማስፋፋት፣ የውጭ ኢንቨስተሮችን ለመለየትና ለመሳብ፣ ቴክኖሎጂን ለማፈላለግ፣ ለመምረጥ እና ለማስገባት፣ የውጭ የልማት ፋይናንስና የቴክኒክ ተራድኦ የሚገኝበትን ሁኔታ ለማመቻቸት፣ ለሚመለከታቸው የመንግስት አስፈፃሚ አካላት ድጋፍ ይሠጣል፤

h) maintain contacts, as may be necessary, with foreign diplomatic and consular representatives in Ethiopia as well as with representatives of international organizations with a view to facilitating the protection of mutual interests;

i) ensure that privileges and immunities accorded to foreign diplomatic missions and representatives of international organizations under international law and treaties to which Ethiopia is a party are respected;

j) coordinate and supervise the activities of Ethiopia's diplomatic and consular missions abroad and permanent missions' offices in international organizations;

k) issue diplomatic and service passports and diplomatic and service entry visas in accordance with the relevant laws;

l) provide support to relevant Government Executive Organs through economic diplomacy to: promote the country's foreign trade and tourism; identify and attract foreign investors; search, choose and cause the transfer of technology; facilitate the mobilization of financial and technical assistance from external sources;

https://chilot.me



ኀ) በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን መብትና ጥቅም እንዲጠበቅ ያደርጋል፤ በኢትዮጵያውያን ማህበረሰብና በኢትዮጵያ ወዳጆች የተመሠረቱ ማህበራትን ያበረታታል፣ ድጋፍ ይሰጣል፤

ነ) የዳያስፖራ ተሳትፎን ለማረጋገጥ የሚሰሩ ሥራዎችን ያስተባብራል፣ ይደግፋል፤ በፕሮቶኮል ጉዳዮች ላይ መረጃዎችንና የምክር አገልግሎቶችን ይሰጣል፤

ኘ) በፐብሊክ ዲፕሎማሲና ኮሙኒኬሽን ተግባራት የሀገር ገጽታን የመገንባትና ደጋፊዎችን የማበራከት ስልቶችን ይነድፋል፣ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፤

፪/ በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች ለውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

## ፵. <u>የፍትሕ ሚኒስቴር</u>

፩/ የፍትሕ ሚኒስቴር የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፱፻፵፫/፪ሺ፰ ላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በሥራ ላይ ያውላል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ፍትሕ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

ሀ) የፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶች እርስ በርሳቸው ባልተግባቡበት የፍትሐ ብሔር ጉዳይ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

m) ensure that the interests and the rights of Ethiopians residing abroad are protected; encourage and support associations formed by Ethiopian communities and friends of Ethiopia;

n) coordinate and support activities which ensure the participation of Ethiopian Diaspora; provide information and advisory service on matters of protocol;

o) design and follow up the implementation of public diplomacy and communication strategies to build the country's image and to rally supporters.

2/ The powers and duties entrusted to Ministry of Foreign Affairs under other laws that are currently in force are hereby vested in the Ministry of Foreign Affairs established by this Proclamation.

## 40. <u>Ministry of Justice</u>

1/ The Ministry of Justice shall implement the provisions provided for in Federal Attorney General Establishment Proclamation No. 943/ 2016.

2/ Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, the Ministry of Justice shall have the following powers and duties:

a) render decision on civil case dispute arising between Federal Government Offices;

https://chilot.me



ለ) በሀገር ውስጥና በውጪ ሀገር የሚገኙ ከወንጀል ጋር የተገናኙ ንብረቶች የማስመለስ ሥራዎችን ይሠራል፣ ያስተባብራል፤

ሐ) በፌደራል ፖሊስ ምርመራ ዘርፍ የሚከናወኑ የምርመራ ሥራዎችን ይመራል፣ ይከታተላል፣ ያስተባብራል፣ ሪፖርት እንዲቀርብለት ያደርጋል፤

መ) በንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር ፰፻፲፫/፪ሺ፮ እና በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን አዋጅ ቁጥር ፭፻፶፩/፲፱፻፺፱ የተመለከቱት የዳኝነት አካላት በሥሩ ሆነው በአዋጆቹ የተመለከቱትን ከዳኝነትና ችሎት ጋር የተያያዙ ድንጋጌዎችን ሥራ ላይ ያውላል፤

ሠ) ታረሚዎችን የማረምና ማነፅ ሥራዎችን፣ በዘርፉ የሚደረጉ ጥናቶችንና የሚሰጡ ሥልጠናዎችን፣ ከግብር ጋር የተያያዙ የይግባኝ ሥራዎቸን፣ የሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ ሥራዎችን እና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን የሚመለከቱ ሥራዎችን ያስተባብራል፡፡

፫/ የፍትሕ ሚኒስትሩ የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ይሆናል፤

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የፍትሕ ሚኒስቴር የወንጀል ጉዳዮች ዐቃቤያነ ሕግ ዘርፍ የአሠራር ነፃነቱ ተጠብቆ በተለይም የወንጀል ክስ፣ የክርክርና የፍርድ ማስፈጸም ሥራዎች ለማከናወን የሚያስችል አደረጃጀትና አሠራር ያለው መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

b) perform and coordinate the functions of recovery of assets related to crimes from domestic and foreign jurisdictions;

c) oversee, follow up and coordinate the criminal investigation function of the Federal Police investigation division and require that a report be submitted to it;

d) bring the adjudicative bodies provided under Trade Practice and Consumers Protection Proclamation No. 813/2014 and Commodity Exchange Authority Establishment Proclamation No. 551/2007 and implement the provisions relating to judicial functions provided thereof;

e) coordinate activities related to rehabilitation of prisoners, conduct of sector-based researches and training, tax appeal, authentication and registration of documents as well as organizations of civil societies.

3/ The Ministry of Justice is the Federal Attorney General.

4/ Without prejudice to Sub-Article (1) and (2) of this Article, the Ministry of Justice shall ensure the existence of a structure and working procedure that enable the criminal prosecution division to maintain its operational independence in carrying out its activities, in particular, criminal prosecution, litigation and execution of judgments.

https://chilot.me



፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች ለጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው ፍትሕ ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

**፵፩. ሰላም ሚኒስቴር**

፩/ የሰላም ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

ሀ) ከሰላም ጋር የተያያዙ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና ሕጎችን ለማውጣት የሚስችሉ ሀሳቦችን ያመነጫል፣ ሲጸድቁም በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የሀገር ውስጥ ሰላምን ለማስጠበቅ አግባብ ካላቸው የፌደራልና የክልል መንግሥታት አካላት ጋር በመተባበር ይሰራል፤ የሀገርና ሕዝብ ሠላም እንዲከበር የሚያስችል ስልት ይነድፋል፤ የግንዛቤና የንቅናቄ ሥራዎችን ያከናውናል፤

ሐ) በተለያዩ ሃይማኖቶችና እምነቶች ተከታዮች፣ እንዲሁም በተለያዩ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መካከል ሰላምና መከባበር እንዲሰፍን ለማድረግ አግባብ ካላቸው የመንግሥት አካላት፣ የባህልና የሃይማኖት ተቋማት እንዲሁም ከሌሎች አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ይሠራል፤

መ) በሃይማኖት፣ በብሔርና ሌሎች ምክንያቶች ሽፋን የሚደረግ የአክራሪነትና የጽንፈኛነትን አስተሳሰብ ለመከላከል የሚያስችሉ ስልቶችን ይቀይሳል፣ ያስፈጽማል፤

5/ Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, the powers and duties entrusted to the Attorney General under other laws that are currently in force are hereby vested in the Ministry of Justice.

**41. Ministry of Peace**

1/ The Ministry of Peace shall have the following powers and duties:

a) initiates ideas to formulate policies, strategies and laws in relation to peace; implement the same upon approval;

b) work, in collaboration with relevant Federal and Regional Government organs to ensure the maintenance of public peace; devise a strategy for protection of public peace; undertake awareness creation and sensitization activities to ensure the same;

c) work, in collaboration with relevant government organs, cultural and religious organizations, and other pertinent bodies, to ensure peace and mutual respect among followers of different religions and beliefs, as well as nations, nationalities and peoples;

d) design and implement strategy to prevent extremism and fanaticism under the cover of religion, nation and other reasons;

https://chilot.me



ሠ) በወሳኝ ሀገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ብሔራዊ መግባባት እንዲፈጠር አግባብነት ያላቸውን አካላት ያስተባብራል፤ የመፍትሄ ሃሳቦችን ለመንግሥት ያቀርባል፤ ሲወሰንም አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

ረ) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ሀገራዊ አንድነትና መግባባትን የሚያጎለብት የባህል ልውውጥ፣ የሥነ-ዜጋ ትምህርት የሚስፋፋበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

ሰ) በሕብረተሰቡ መካከል የሰላም፣ የመከባበርና የመቻቻል ባህል እንዲዳብር የግንዛቤና ንቅናቄ ስልቶችን ይቀይሳል፣ አተገባበሩን ይከታተላል፤

ሸ) ለአካባቢያዊ ግጭቶች መንስዔ የሆኑ ጉዳዮችን በጥናት ይለያል፤ ኅብረተሰቡ ወደ ግጭትና አለመረጋጋት እንዳያመራ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን የሚያመለክት ጥናት ያቀርባል፣ ሲወሰንም ተግባራዊ ያደርጋል፤

ቀ) በፌደራል መንግሥትና በክልሎች መካከል በመግባባትና በአጋርነት ላይ የተመሠረተ መልካም ግንኙነትና ትብብር እንዲኖር በማድረግ የፌደራል ሥርዓቱ እንዲጠናከር የግንኙነቱ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፤

በ) በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ ፵፰ እና ፷፪ ንዑስ አንቀጽ (፮) እንዲሁም ሌሎች አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ በክልሎች መካከል የሚነሱ አለመግባባቶች የሚፈቱባቸውን ሁኔታዎች ያመቻቻል፤

e) coordinate the relevant organs to bring about consensus on critical national issues; submit recommendations to the government and follow up their implementation upon approval;

f) promote, in collaboration with concerned organs, the enhancement of cultural exchange, civic education, and artistic works that build national unity and consensus;

g) devise strategy for awareness creation and sensitization that to foster a culture of respect and tolerance among communities, and follow up their implementation;

h) identify causes of conflicts among local communities through study; submit a study proposing recommendations to keep communities away from conflicts and instability, and implement the same upon approval;

i) serve as a focal point to strengthen the federal system by cultivating good relationship and cooperation between the Federal Government and Regions based on mutual understanding and partnership;

j) without prejudice to the provisions of Article 48 and Sub-Article (6) of Article 62 of the Constitution and other relevant provisions, facilitate the resolution of disputes arising between regions;

https://chilot.me


ተ) አግባብነት ያላቸው ሕጎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ከክልሎች ጥያቄ ሲቀርብ በክልሎች ውስጥ የሚፈጠሩ አለመግባባቶችና ግጭቶች በዘላቂነት የሚፈቱበትን መፍትሔ ይቀይሳል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤

ቸ) የፌደራል መንግሥቱ በክልሎች ጉዳይ ጣልቃ እንዲገባ ሲወሰን አፈጻጸሙን ያስተባብራል፤

ኀ) የሃይማኖት ድርጅቶችን ይመዘግባል፤

፪/ በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች፣ በዚህ አዋጅ ከተሰጠው ሥልጣንና ተግባር ጋር ግንኙነት ያላቸው ለሰላም ሚኒስቴር የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው ሰላም ሚኒስቴር ተሰጥተዋል።

k) without prejudice to relevant laws, design, upon the request of the Region, solutions that enable sustainably resolve misunderstandings and conflicts; implement the same;

l) coordinate the implementation of decisions authorizing the intervention of the Federal Government in the affairs of regions;

m) register religious organizations;

2/ The powers and duties entrusted to the Ministry of Peace in relation to the powers and duties entrusted to it under this Proclamation and under other laws that are currently in force are hereby vested in the Ministry of Peace established by this Proclamation.

## ክፍል አምስት
## ስለ ሌሎች አስፈጻሚ አካላት

### ፵፪. የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን

፩/ የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግስት አስፈጻሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

፪/ የኮሚሽኑ አደረጃጀት እና ሥልጣንና ተግባራት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ይወሰናል፡፡

### ፵፫. የመንግስት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት

፩/ የመንግስት ኮሚኒኬሽን አገልግሎት ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግስት አስፈጻሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

፪/ የአገልግሎቱ አደረጃጀት እና ሥልጣንና ተግባራት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ይወሰናል፡፡

## PART FIVE
## OTHER EXECUTIVE ORGANS

### 42. Civil Service Commission

1/ The Civil Service Commission is hereby established as an autonomous federal government organ having its own legal personality;

2/ The powers, duties and organization of the Commission shall be determined by Council of Ministers Regulation.

### 43. Government Communication Service

1/ The Government Communication Service is hereby established as an autonomous federal government organ having its own legal personality;

2/ The powers, duties and organization of the Service shall be determined by Council of Ministers Regulation.

https://chilot.me


**፵፬. <u>ጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት</u>**

፩/ ጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግስት አስፈጻሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

፪/ የጽህፈት ቤቱ አደረጃጀት እና ሥልጣንና ተግባራት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ይወሰናል፡፡

**፵፭. <u>የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን</u>**

፩/ የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግስት አስፈጻሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

፪/ የባለስልጣኑ አደረጃጀት እና ሥልጣንና ተግባራት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ይወሰናል፡፡

**፵፮. <u>የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት</u>**

፩/ የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግስት አስፈጻሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

፪/ የኢንስቲትዩቱ አደረጃጀት እና ሥልጣንና ተግባራት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ይወሰናል፡፡

**፵፯. <u>የእንስሳት ልማት ኢንስቲትዩት</u>**

፩/ የእንስሳት ልማት ኢንስቲትዩት ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግስት አስፈጻሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

፪/ የኢንስቲትዩቱ አደረጃጀት እና ሥልጣንና ተግባራት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ይወሰናል፡፡

**44. <u>Prime Minister Office</u>**

1/ The Prime Minister Office is hereby established as an autonomous federal government organ having its own legal personality;

2/ The powers, duties and organization of the Office shall be determined by Council of Ministers Regulation.

**45. <u>Ethiopian Agricultural Authority</u>**

1/ The Ethiopian Agricultural Authority is hereby established as an autonomous federal government organ having its own legal personality;

2/ The powers, duties and organization of the Authority shall be determined by Council of Ministers Regulation.

**46. <u>Ethiopian Veterinary Institute</u>**

1/ Ethiopian Veterinary Institute is hereby established as an autonomous federal government organ having its own legal personality;

2/ The powers, duties and organization of the Institute shall be determined by Council of Ministers Regulation.

**47. <u>Livestock Development Institute</u>**

1/ Livestock Development Institute is hereby established as an autonomous federal government organ having its own legal personality;

2/ The powers, duties and organization of the Institute shall be determined by Council of Ministers Regulation.

https://chilot.me


**፵፰. የኢትዮጵያ ደን ልማት**

፩/ የኢትዮጵያ ደን ልማት ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግስት አስፈጻሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

፪/ የልማቱ አደረጃጀት እና ሥልጣንና ተግባራት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ይወሰናል፡፡

**፵፱. የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት**

፩/ የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግስት አስፈጻሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

፪/ የልማቱ አደረጃጀት እና ሥልጣንና ተግባራት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ይወሰናል፡፡

**፶. የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት**

፩/ የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግስት አስፈጻሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

፪/ የኢንስቲትዩቱ አደረጃጀት እና ሥልጣንና ተግባራት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ይወሰናል፡፡

**፶፩. የነዳጅ እና ኤነርጂ ባለስልጣን**

፩/ የነዳጅ እና ኤነርጂ ባለስልጣን ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግስት አስፈጻሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

፪/ የባለስልጣኑ አደረጃጀት እና ሥልጣንና ተግባራት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ይወሰናል፡፡

**48. Ethiopian Forest Development**

1/ Ethiopian Forest Development is hereby established as an autonomous federal government body having its own legal personality;

2/ The powers, duties and organization of the Development shall be determined by Council of Ministers Regulation.

**49. Ethiopian Enterprise Development**

1/ Ethiopian Enterprise Development is hereby established as an autonomous federal government body having its own legal personality;

2/ The powers, duties and organization of the Development shall be determined by Council of Ministers Regulation.

**50. Manufacturing Industry Development Institute**

1/ Manufacturing Industry Development Institute is hereby established as an autonomous federal government body having its own legal personality;

2/ The powers, duties and organization of the Institute shall be determined by Council of Ministers Regulation.

**51. Petroleum and Energy Authority**

1/ Petroleum and Energy Authority is hereby established as an autonomous federal government body having its own legal personality;

2/ The powers, duties and organization of the Authority shall be determined by Council of Ministers Regulation.

https://chilot.me



**፶፪. <u>የማዕድን ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት</u>**

፩/ የማዕድን ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግስት አስፈጻሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

፪/ የኢንስቲትዩቱ አደረጃጀት እና ሥልጣንና ተግባራት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ይወሰናል፡፡

**፶፫. <u>የመንግስት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር</u>**

፩/ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግስት አስፈጻሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

፪/ የአስተዳደሩ አደረጃጀት እና ሥልጣንና ተግባራት በደንብ ቁጥር ፬፻፵፭/፪ሺ፲፩ ላይ የተደነገገው ይሆናል፤

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፪) ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አስተዳደሩ የኢትዮጵያ ፐልፕና ወረቀት አክሲዮን ማህበርን እና የኢትዮጵያ ሎተሪ አገልግሎት ጨምሮ ሁሉንም በአዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሰረት ተቋቁመው በሥራ ላይ ያሉትን የመንግስት ልማት ድረጅቶችን ያስተዳድራል፤

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፫) ላይ የተደነገገው ቢኖርም በዚህ አዋጅ ለተመለከቱ አስፈጻሚ አካላት ተጠሪ የተደረጉ የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተጠሪ በተደረጉላቸው አስፈጻሚ አካላት ይተዳደራሉ፤

**52. <u>Mineral Industry Development Institute</u>**

1/ Mineral Industry Development Institute is hereby established as an autonomous federal government body having its own legal personality;

2/ The powers, duties and organization of the Institute shall be determined by Council of Ministers Regulation.

**53. <u>Public Enterprises Holding and Administration</u>**

1/ Public Enterprises Holding and Administration is hereby established as an autonomous federal government body having its own legal personality;

2/ The powers, duties and organization of the institute shall be as provided for under Regulation No. 445/2019;

3/ Without prejudice to Sub-Article (2) of this Article, the Administration shall administer public enterprises established under Proclamation No. 25/1992 including Ethiopian Pulp and Paper Share Company and National Lottery Service;

4/ Notwithstanding Sub-Article (3) of this Article, public enterprises indicated in this Proclamation shall be administered by those Executive Organs that made accountable them.

https://chilot.me



## ፶፬. የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ

፩/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፫ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ የሕግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግስቱ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፣

፪/ የሆልዲንጉ ዓላማ የመንግስት የልማት ድርጅቶችንና ሌሎች በፌደራል መንግስት ሥር የሚገኙ ሀብቶችን በባለቤትነት ማስተዳደር እና የመንግስትን ሀብት በአግባቡ በመጠቀም የኢንቨስትመንት ውጤታማነትን ለማሳደግ እንዲሁም ተጨማሪ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ እንደስትራቴጂያዊ መሳሪያ በመሆን ማገልገል ነው፤

፫/ የሆልዲንጉ ሥልጣንና ተግባርና አደረጃጀት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ የሚወሰን መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣የመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬፣ የመንግሥት የልማት ድርጀቶችን ወደ ግል ስለማዛወር የወጣ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፮/፪ሺ፲፪፣ ቢኖርም በመንግስት የሚመደብለትን ንብረትነታቸው የመንግስት የሆኑ ሃብቶች ተረክቦ ያስተዳድራል፤ በሥሩ ተቀጥላ ድርጅቶች የሚቋቋሙበትን ሁኔታ ይወስናል፤በባለቤትነት የያዛቸውን ተቀጥላ ኩባንያዎች የካፒታል እድገት ወይም ቅነሳ፣ ሽያጭ፣ ጥምረት፣ ክፍፍል፣ ምስረታ፣ ወይም አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ተቀጥላ ኩባንያዎችን በመውሰድ ወይም እንደ አዲስ ስለማቋቋም የቅድመ ዝግጅት ሥራ ያከናውናል፣ ይወስናል፥ ንዑስ ፈንዶች የሚቋቋሙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ በተቋቋመ ድርጅት ውስጥ ብቻውን ወይም ከሀገር ውስጥ ወይም ከወጪ ሀገር ኢንቬስተሮች ጋር

## 54. Ethiopian Investment Holdings

1/ Notwithstanding the provisions of Article 53 of this Proclamation, the Ethiopian Investment Holdings is hereby established as the federal government body having its own legal personality.

2/ The Ethiopian Investment Holdings has the objective of optimize investment value through effective ownership and management of state-owned enterprises and other assets under the federal government; as well as serve as a strategic investment arm of the government of Ethiopia through attraction of more investment.

3/ Without prejudice to the Regulation of the Council of Ministers stipulating the powers, duties and organization of the Holdings; and irrespective of the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992 and the Public Enterprises Privatization Proclamation No. 1206/2020; the Ethiopian Investment Holdings shall takeover and manage state-owned assets that may be assigned to it by the government; establish subsidiaries; decide on its subsidiaries’ increase or reduction of capital, sale, amalgamation, division, spin-off, or any other restructuring, either by taking over one or more subsidiary companies or by the formation of a new company; establish sub-funds or acquire share in existing entities or funds solely or in association with local or foreign investors; perform

https://chilot.me


በመሆን በጋራ አክሲዮኖችን ይይዛል፤ ሌሎች ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሥራዎችን ይሰራል::

other activities necessary for the attainment of its objectives.

## ፶፭. የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት

፩/ የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግስት አስፈጻሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

፪/ የኢንስቲትዩቱ አደረጃጀት እና ሥልጣንና ተግባራት በሚኒስተሮች ምክር ቤት ደንብ ይወሰናል፡፡

## 55. Policy Studies Institute

1/ Policy Studies Institute is hereby established as an autonomous federal government body having its own legal personality;

2/ The powers, duties and organization of the Institute shall be determined by Council of Ministers Regulation.

## ፶፮. የኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት

፩/ የኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግስት አስፈጻሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

፪/ አገልግሎቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

ሀ) በኢትዮጵያ የስታቲስቲክስ ሥርዓት፣ ስታንደርድ እና ደንብ መሠረት በሰርቬይ፣ በቆጠራ፣ በምዝገባና ከአስተዳደር መዛግብት እና በሌሎች የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ የስታቲስቲክስ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ የተሰበሰቡ መረጃዎችን ያደራጃል፣ በፕላንና ልማት ሚኒስቴር የመረጃ ጥራት ዕውቅና ሲያገኝ መረጃዎቹን እንደ ኦፊሴላዊ ስታቲስቲክስ ያሰራጫል፤

ለ) የመንግስት መስሪያ ቤቶች እና ሌሎች አካላት የስታቲስቲክስ መዝገብና መረጃ አያያዝ፣ የማያቋርጥ የምዝገባ አሠራርና የሪፖርት ሥርዓት እንዲዘረጉ የቴክኒክ ምክርና አቅም የመገንባት ድጋፍ ያደርጋል፤

## 56. Ethiopian Statistical Service

1/ The Ethiopian Statistical Service is hereby established as an autonomous federal government body having its own legal personality;

2/ The Service shall have the following powers and duties:

a) collect statistical data in accordance with Ethiopian statistical system, standard and regulation through sample surveys, censuses, registration and administrative records and other methods of data collection; compile, organize and disseminate same as official statistics once data quality assurance and clearance is approved by the Ministry of Planning and Development;

b) provide technical advice and support on capacity building for government organs and other bodies on statistical record and data reporting system;

https://chilot.me



ሐ) ከመንግስታዊ የመረጃ አሰባሰብ ግዴታ እና ኃላፊነት ውጪ፣ በሀገር ውስጥ ወይም በዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጥያቄ ሲቀርብለት መረጃ የመሰብሰብና የማቀነባበር አገልግሎት ይሰጣል፤

መ) ኦፊሴላዊ ስታቲስቲክስ ወጥና በታለመለት የጊዜ ሠሌዳ እንዲሰበሰብ ያደርጋል፤ የኦፊሴላዊ ስታቲስቲክስን ጥራትንና ተዓማኒነትን ለማጎልበት የሚረዱ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎችን እና መሳሪያዎችን ለማሻሻል የስታቲስቲክስ መረጃ ጥናት ዘዴ ምርምር ያካሂዳል፤

ሠ) ዘመናዊ የመረጃ አሰባሰብ ቴክኖሎጂና መሣሪያዎችን በመጠቀም መረጃን ይሰበስባል፣ ያከማቻል፣ ያሰራጫል፣

ረ) ከስፔስ ሳይንስና ጂኦስፓሻል ኢንስቲትዩት ጋር በመቀናጀት ዘመናዊ የመረጃ አሰባሰብ ቴክኖሎጂና መሣሪያዎችን በመጠቀም የጂኦስፓሻል መረጃዎችን ይሰበስባል፤ በሌሎች የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተሰበሰቡትን የስታቲስቲክስ መረጃዎችን ወደ ዲጂታል እና ጂኦስፓሻል የመረጃ ቅርጸነት ይቀይራል፤

ሰ) ከደኅንነት እና ምስጢራዊ መረጃዎች በስተቀር፣ ማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ዋና የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ እና የሥነ-ሕዝብ አወቃቀር መረጃ ሰብሳቢ ሆኖ አገልግሎት ይሰጣል፤

ሸ) ሀገራዊ የስታቲስቲክስ መረጃ ማከማቻ ማዕከል በመሆን ያገለግላል፤ የመረጃ ማከማቻ ቋት በዋና መስሪያ ቤት ያደራጃል፣ በየጊዜውም ያሻሽላል፤

c) provide data collection and arrangement service to national and international non-governmental organizations upon request with the exception of its official duty and responsibility;

d) cause the collection of official statistical data in a consistent manner and as per the set schedule; carry out research and study on data collection methodology and tools that promote the quality and credibility official statistics;

e) collect, compile and disseminate statistical data by using modern data collection methods and tools;

f) collect, in coordination with Space Science and Geospatial Institute, geospatial data by using modern data collection tools; convert statistical data to digital and geospatial data format;

g) provide data collection service as the main data collector of economic, social and demographic data;

h) serve as national statistical data storage center; organize data storage center at the head office; improve database capacity from time to time;

https://chilot.me


ቀ) የስታቲስቲክስ መረጃ አሰባሰብ ዘዴዎችን በተመለከተ ጥናትና ምርምር ያከናውናል፣ የተገኙ ውጤቶችንም በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤

በ) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የስታቲስቲክስ ማስተዋወቅ ተግባራትን ያከናውናል፤ የስታቲስቲክስ የአቅም ግንባታ ሥልጠና ይሰጣል፤

ተ) ክልሎች ጥያቄ ሲያቀርቡ አስፈላጊውን የስታቲስቲክስ መረጃ የመሰብሰብ፣ የማደራጀት፣ የመተንተንና በጽሁፍ የማውጣትና የማሰራጨት ዝግጅትን በመምራትና ማስተባበር ረገድ ያግዛል፣ የስታቲስቲክስ መዝግብ አያያዝ ሥርዓት መቋቋሙን ያረጋግጣል፤

ቸ) ሀገራዊ የስታቲስቲክስ አቅም ለመገንባት ከልማት አጋሮች የገንዘብ፣ የቁሳዊና ቴክኒክ እርዳታ የሚገኝበትን ሁኔታ በማመቻቸት ለፕላንና ልማት ሚኒስቴር ያቀርባል፣ ሲጸደቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

ኀ) በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ በሚወሰነው መሠረት ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች ክፍያ ያስከፍላል፤

ነ) በስታስቲክስና ተመሳሳይ ዘርፍ ከተቋቋሙ ሀገራዊ የሙያ ማህበራት ጋር ትብብር ይፈጥራል፣ እንደአስፈላጊነቱ ኮንፈረንሶች በሚሰጡበት ጊዜ አስፈላጊ እርዳታዎችን ይሰጣል፤

ኘ) በአዋጅ ቁጥር ፬፻፵፪/፲፱፻፺፯ አንቀጽ ፲፯ ላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በሥራ ላይ ያውላል፡፡

i) conduct research and study on statistical data collection methods; cause the implementation of the findings of the same;

j) perform, in collaboration with the concerned organs, the function of statistical advocacy; provide capacity building training on statistics;

k) provide assistance, upon request from regional governments, in guiding and coordinating the collection, compilation and analysis of statistical data and publication and dissemination of the same; ensure the establishment of statistical registration system;

l) facilitate conditions for soliciting financial, material and technical support from development partners for building national statistical capacity and implement same upon approval by the Ministry of Planning and Development;

m) charge fee for the services it renders in accordance with Regulation to be issued by Council of Ministers;

n) establish cooperation with national professional associations in the fields of statistics and related disciplines and sponsor statistical conferences as appropriate;

o) implement the provision of Article 17 of Proclamation No.442/2005.

https://chilot.me


**፶፯. <u>የስፔስ ሳይንስና ጂኦስፓሻል ኢንስቲትዩት</u>**

፩/ የስፔስ ሳይንስና ጂኦስፓሻል ኢንስቲትዩት ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግስት አስፈጻሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

፪/ የኢንስቲትዩቱ አደረጃጀት እና ሥልጣንና ተግባራት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ይወሰናል፡፡

**፶፰. <u>የኢትዮጵያ ቴክኖሎጂ ባለስልጣን</u>**

፩/ የኢትዮጵያ ቴክኖሎጂ ባለስልጣን ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግስት አስፈጻሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

፪/ የባለስልጣኑ አደረጃጀት እና ሥልጣንና ተግባራት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ይወሰናል፡፡

**፶፱. <u>የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን</u>**

፩/ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግስት አስፈጻሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

፪/ የባለስልጣኑ አደረጃጀት እና ሥልጣንና ተግባራት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ይወሰናል፡፡

**፷. <u>የትምህርትና ሥልጠና ባለስልጣን</u>**

፩/ የትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግስት አስፈጻሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

፪/ የባለስልጣኑ አደረጃጀት እና ሥልጣንና ተግባራት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ይወሰናል፡፡

**57. <u>Space Science and Geospatial Institute</u>**

1/ The Space Science and Geospatial institute is hereby established as an autonomous federal government organ having its own legal personality;

2/ The powers, duties and organization of the Institute shall be determined by Council of Ministers Regulation.

**58. <u>Ethiopian Technology Authority</u>**

1/ The Ethiopian Technology Authority is hereby established as an autonomous federal government organ having its own legal personality;

2/ The powers, duties and organization of the Authority shall be determined by Council of Ministers Regulation.

**59. <u>Environment Protection Authority</u>**

1/ The Environment Protection Authority is hereby established as an autonomous federal government body having its own legal personality;

2/ The powers, duties and organization of the Authority shall be determined by Council of Ministers Regulation.

**60. <u>Education and Training Authority</u>**

1/ Education and Training Authority is hereby established as an autonomous federal government body having its own legal personality;

2/ The powers, duties and organization of the Authority shall be determined by Council of Ministers Regulation.

https://chilot.me



**፷፩. <u>የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ኢንስቲትዩት</u>**

፩/ የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ኢንስቲትዩት ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግስት አስፈጻሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

፪/ የኢንስቲትዩቱ አደረጃጀት እና ሥልጣንና ተግባራት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ይወሰናል፡፡

**፷፪. <u>የውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት</u>**

፩/ የውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግስት አስፈጻሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

፪/ የኢንስቲትዩቱ አደረጃጀት እና ሥልጣንና ተግባራት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ይወሰናል፡፡

**፷፫. <u>የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት</u>**

፩/ የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግስት አስፈጻሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

፪/ አገልግሎቱ በደንብ ቁጥር ፬፻፵፱/፪ሺ፲፩ ለኢሚግሬሽን፣ ዜግነትና ወሳኝ ኩነቶች ኤጀንሲ የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራትን በሥራ ላይ ያውላል፡፡

**፷፬. <u>የስደተኞችና ተመላሾች አገልግሎት</u>**

፩/ የስደተኞችና ተመላሾች አገልግሎት ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግስት አስፈጻሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

፪/ የአገልግሎቱ አደረጃጀት እና ሥልጣንና ተግባራት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ይወሰናል፡፡

**61. <u>Technical and Vocational Training Institute</u>**

1/ Technical and Vocational Training Institute is hereby established as an autonomous federal government body having its own legal personality;

2/ The powers, duties and organization of the Institute shall be determined by Council of Ministers Regulation.

**62. <u>Institute of Foreign Affairs</u>**

1/ Institute of Foreign Affairs is hereby established as an autonomous federal government body having its own legal personality;

2/ The powers, duties and organization of the Institute shall be determined by Council of Ministers Regulation.

**63. <u>Immigration and Citizenship Service</u>**

1/ Immigration, and Citizenship Service is hereby established as an autonomous federal government body having its own legal personality;

2/ The service shall implement the powers and duties entrusted to Immigration, Nationality and Vital Registration Agency under Regulation No. 449/2019.

**64. <u>Refugees and Returnees Service</u>**

1/ The Refugees and Returnees Service is hereby established as an autonomous federal government body having its own legal personality;

2/ The powers, duties and organization of the service shall be determined by Council of Ministers Regulation.

https://chilot.me


**፷፭. <u>የኢትየጵያ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን</u>**

፩/ የኢ.ትዮጵያ የኮንስትራክሽን ባለስልጣን ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግስት አስፈጻሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

፪/ የባለስልጣኑ አደረጃጀት እና ሥልጣንና ተግባራት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ይወሰናል፡፡

**፷፮. <u>የኢ.ትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለስልጣን</u>**

፩/ የኢ.ትዮጵያ የምግብ እና መድኃኒት ባለስልጣን ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግስት አስፈጻሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

፪/ የባለስልጣኑ አደረጃጀት እና ሥልጣንና ተግባራት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ይወሰናል፡፡

**፷፯. <u>የኢ.ትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን</u>**

፩/ የኢ.ትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግስት አስፈጻሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

፪/ የኮሚሽኑ ሥልጣንና ተግባር እና አደረጃጀት በደንብ ቁጥር ፬፻፴፯/፪ሺ፲፩ ላይ የተደነገገው ይሆናል፡፡

**፷፰. <u>የኢ.ትዮጵያ ጂኦሎጂካል ኢ.ንስቲትዩት</u>**

፩/ የኢ.ትዮጵያ ጂኦሎጂካል ኢ.ንስቲትዩት ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግስት አስፈጻሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

፪/ የኢ.ንስቲትዩቱ ሥልጣንና ተግባር እና አደረጃጀት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ይወሰናል፡፡

**65. <u>Ethiopian Construction Authority</u>**

1/ The Ethiopian Construction Authority is hereby established as an autonomous federal government body having its own legal personality;

2/ The powers, duties and organization of the Authority shall be determined by Council of Ministers Regulation.

**66. <u>Ethiopian Food and Drug Authority</u>**

1/ The Ethiopian Food and Drug Authority is hereby established as an autonomous federal government body having its own legal personality;

2/ The powers, duties and organization of the Authority shall be determined by Council of Ministers Regulation.

**67. <u>Ethiopian Customs Commission</u>**

1/ The Ethiopian Customs Commission is hereby established as an autonomous federal government body having its own legal personality;

2/ The powers, duties and organization of the Commission shall be as provided for under Regulation No. 437/2018.

**68. <u>Ethiopian Geological Institute</u>**

1/ The Ethiopian Geological Institute is hereby established as an autonomous federal government body having its own legal personality;

2/ The powers, duties and organization of the Institute shall be determined by the Council of Ministers Regulation.

https://chilot.me



**፷፱. <u>የኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት</u>**

፩/ የኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግስት አስፈጻሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

፪/ የአገልግሎቱ ሥልጣንና ተግባር እና አደረጃጀት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ይወሰናል፡፡

**፸. <u>የኢትዮጵያ የአደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን</u>**

የኢትዮጵያ የአደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን በሥራ ላይ ባሉ ሕጎችና ድንጋጌዎች ከተሠጡት ሥልጣንና ተግባራት በተጨማሪ የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት ኤጀንሲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፹፬/፪ሺ፲፫ የስትራቴጂክ ለመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደር የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት ሁሉ በዚህ አዋጅ ለኢትዮጵያ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን ተሰጥተዋል።

**፸፩. <u>የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር</u>**

፩/ የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግስት አስፈጻሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

፪/ አስተዳደሩ በመንገድ ፈንድ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፷፮/፲፱፻፹፱ ለመንገድ ፈንድ ጽህፈት ቤት የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራትን በሥራ ላይ የሚያውል መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ሥልጣንና ተግባሩ እና አደረጃጀት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ይወሰናል፡፡

**69. <u>Ethiopian Pharmaceutical Supply Service</u>**

1/ The Ethiopian Pharmaceutical Supply Service is hereby established as an autonomous federal government body having its own legal personality;

2/ The powers, duties and organization of the Service shall be determined by the Council of Ministers Regulation.

**70. <u>Ethiopian Disaster Risk Management Commission</u>**

In addition to the powers and duties given to National Disaster Risk Management Commission under existing laws, the powers and duties given to the Emergency Food Security Reserve Administration under Council of Ministers Regulations Number 284/2013 are hereby vested in the Commission.

**71. <u>Ethiopian Roads Administration</u>**

1/ The Ethiopian Roads Administration is hereby established as an autonomous federal government body having its own legal personality;

2/ In Addition to implementing the powers and functions entrusted to Road Fund Office under Proclamation No 66/1997, the powers, duties and organization of the Administration shall be determined by the Council of Ministers Regulation.

https://chilot.me


**፸፪. የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂካል ኢንስቲትዩት**

የኢትዮጵያ ሜትዎሮሎጂካል ኢንስቲትዩት በሌሎች ሕጎች የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው የሚከተሉትን ሥልጣንና ተግባራት ያከናውናል፡-

፩/ የሚቲዎሮሎጂ እና የአየር ጠባይ አገልግሎት ይሰጣል፤

፪/ ሀገራዊ የአየር ጠባይ አገልግሎትን ይመራል፣ ያስተባብራል፣ የሚቲዎሮሎጂ እና የአየር ጠባይ ለውጥ ላይ ጥናትና ምርምር ያካሂዳል፣

፫/ ሚቲዎሮሎጂ እና የአየር ጠባይ ለውጥን በተመለከተ ኢትዮጵያ የፈረመቻቸውን ዓለም አቀፍ ግዴታዎችን እና የሚገኙ ድጋፎችን ይተገብራል፤

፬/ የኢትዮጵያ የአየር ጠባይ የመላመድ እና ስርየት ሥራን ይመራል፣ ያስተባብራል፤

፭/ የሚቲዎሮሎጂ፣ የአየር ብክለት እና የአየር ጠባይ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ይተነትናል፣ ይተነብያል፤

፮/ የአየር ሁኔታ፣ የአየር ጠባይ እና የአየር ጠባይ ለውጥን አስመልክቶ ትምህርታዊ መግለጫ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና የምክር አገልግሎት ይሰጣል፤

፯/ የሚቲዎሮሎጂ መረጃ ለመሰብሰብና ለመጠቀም የሚቀርቡ ጥያቄዎችን መርምሮ ፈቃድ ይሰጣል::

**፸፫. የኢንተርፕሬነርሺፕ ልማት ኢንስቲትዩት**

፩/ የኢንተርፕሬነርሺፕ ልማት ኢንስቲትዩት ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግስት አስፈጻሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

፪/ የኢንስቲትዩቱ አደረጃጀት እና ሥልጣንና ተግባራት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ይወሰናል፡፡

**72. Ethiopian Meteorological Institute**

The Ethiopian Meteorological Institute shall, without prejudices to the powers and duties entrusted to it by other laws, have the following powers and duties:

1/ Provide meteorological and climate related services;

2/ lead national climate services;conduct study and research on meteorological and climate change;

3/ Execute the international obligations signed by Ethiopia with respect to meteorological and climate change; implement supports;

4/ Lead and coordinate Ethiopian climate change adaptation and mitigation activities;

5/ collect, analyses and forecast meteorological, air pollution and climate change information;

6/ provide educational information, early warning and advisory services with respect to weather condition, climate and climate change

7/ examine requests for collection of meteorological information and issue permit for same.

**73. Ethiopian Entrepreneurship Development**

1/ The Ethiopian Entrepreneurship Development is hereby established as an autonomous federal government body having its own legal personality;

2/ The powers, duties and organization of the Development shall be determined by the Council of Ministers Regulation.

https://chilot.me



**፸፬. <u>የመከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ግሩፕ</u>**

፩/ የመከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ግሩፕ ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግስት አስፈጻሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

፪/ የግሩፑ አደረጃጀት እና ሥልጣንና ተግባራት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ይወሰናል፡፡

**፸፭. <u>የመከላከያ ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ ግሩፕ</u>**

፩/ የመከላከያ ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ ግሩፕ ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግስት አስፈጻሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

፪/ የግሩፑ አደረጃጀት እና ሥልጣንና ተግባራት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ይወሰናል፡፡

**፸፮. <u>የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ታለንት ልማት ኢንስቲቲዩት</u>**

፩/ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ታለንት ልማት ኢንስቲትዩት ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግስት አስፈጻሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

፪/ የኢንስቲትዩቱ አደረጃጀት እና ሥልጣንና ተግባራት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ይወሰናል፡፡

**74. <u>Defense Construction Industry Group</u>**

1/ The Defense Construction Industry Group is hereby established as an autonomous federal government body having its own legal personality.

2/ The powers, duties and organization of the Group shall be determined by the Council of Ministers Regulation.

**75. <u>Defense Engineering Industry Group</u>**

1/ The Defense Engineering Industry Group is hereby established as an autonomous federal government body having its own legal personality.

2/ The powers, duties and organization of the Group shall be determined by the Council of Ministers Regulation.

**76. <u>Innovation and Technology Gifted and Talented Development institute</u>**

1/ The Ethiopian Innovation and Technology Gifted and Talented Development institute is hereby established as an autonomous federal government body having its own legal personality,

2/ The powers, duties and organization of the institute shall be determined by the Council of Ministers Regulation.

https://chilot.me


## ክፍል ስድስት

## በሚኒስቴር መስሪያ ቤት ወይም ሌላ አስፈጻሚ አካል እና በተጠሪ ተቋማት መካከል ስለሚኖር ግንኙነት እንዲሁም አስፈጻሚ አካላትን እንደገና ስለማደራጀት

### ፸፯. በሚኒስቴር መስሪያ ቤት ወይም ሌላ አስፈጻሚ አካል እና በተጠሪ ተቋም መካከል ስለሚኖር ግንኙነት

፩/ ለሚኒስቴር መስሪያ ቤት ወይም ለሌላ አስፈጻሚ አካል ተጠሪ የሆነ ተቋም በሕግ የተቋቋመ ራሱን የቻለ ተቋም በመሆኑ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ወይም ሌላ አስፈጻሚ አካል የተጠሪ ተቋሙን ሥራዎች ከመምራት፣ ከማስተባበርና ከመደገፍ ውጪ በእለት ከእለት እንቅስቃሴው ላይ ጣልቃ አይገባም፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ወይም ሌላው አስፈጻሚ አካል ዕቅድና ሪፖርት የተጠሪ ተቋሙንም ዕቅድና ሪፖርት የያዘ መሆን ይኖርበታል፡፡

፫/ በሕግ በሚዘረጋ ሥርዓት መሠረት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ወይም ሌላው አስፈጻሚ አካል የተጠሪ ተቋምን የሰው ኃይል አስተዳደር፣ የፋይናንስ አስተዳደርና መሰል ሥራዎችን ሊያከናውን ይችላል፡፡

፬/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) አፈጻጸም "መምራት፣ ማስተባበርና መደገፍ"፡-

ሀ) የተጠሪ ተቋማትን ዕቅድና የአፈጻጸም ሪፖርት አጠቃላይ አፈጻጸም መከታተልን፣

## PART SIX

